





# ፲፪



## ገርማሜ ንዋይ
## 1916–1953
## "ጾመኛው አገረ-ገዥ"

ብንሸነፍም ብንሞትም እንኳ በዚህች
ሐሰት በበዛባት ምድር ቢያንስ ቢያንስ
ቅንጣት እውነት ይነገር ዘንድ  አባክህ
ታሪካችንን ለዐለም ሁሉ ንገርልን

የሰው ልጅ ራሱን ነጻ ለማውጣት መሰሎቹን በጉራዝ ብርሃን ሲፈልግ፣ በተማሰለት አዘቅት ውስጥ ሊወድቅ ይችላል። ሆኖም ግን ከዚህን መሰሉ ራስን ነጻ የማውጣት ድርጊት ርቆ ከመኖር ለትውልዱ መሻሻል መሥዋዕት መሆንን መምረጥ አለበት። ... ሰው ሐሳቡንና ዐላማውን አዋሕዶ ከህብረቱ ስቡ ጋር በመታገል መሠረታዊ የለውጥ ግድብ ቢገነባ፣ ትግባሩን የቀለለ ያደርገዋል። በዚህ ረገድ የትብብሩ ሐሳብ ቢከሽፍም እንኳ፤ ዛሬ ለትግል የተነሣበት ዐላማ ግብ ተፈጽሞ የሚያየው፤ እሱን ከሠዋው ትውልድ አብራክ ፈልቆ በሚተካው ትውልድ ነው።

ገርማሜ ንዋይ

መቼም በ1950ዎቹ መካከልና መገባደጃዎቹ ላይ ያሉት ዓመታት ዓለማችን በርካታ የለውጥ እንቅስቃሴዎችን ያስተናገደችባቸው ዓመታት ናቸው። የጊዜው ኀያላን አገሮች አሜሪካና ሩሲያ በቀዝቃዛው ጦርነት የኑክለየር መሣሪያ ፉክክር በእጅጉ የታየበት ከመሆኑም ባሻገር፣ በሩሲያዊው ዩሪ ጋጋሪን ፉና ወጊነትና በአሜሪካዊው ኒል አርምስትሮንግ ተከታይነት የጨረቃ ላይ ጉዞ የተጧጧፈባቸው ዓመታት ነበሩ። በፈረንጆቹ 60ዎቹና በኢትዮጵያውያን 50ዎቹ ዓመታት በአሜሪካ በንማርቲን ሉተር ኪንግ መሪነት «ራእይ አለኝ» በሚል መፈክር የሲቪል መብት ትግል ንሮባቸው ያለፉ ዓመታት ናቸው። እስያም በማኦ ዜዱንግ መሪነት የሕዝባዊት ሪፐብሊክ ቻይናን የባህል አብዮት ያስተናገደችበት ጊዜ ነበር። በመሠረቱ በአህጉራችን አፍሪካም ብዙ አገሮች የቅኝ አገዛዝን ቀንበር አሽቀንጥረው በመጣል የነጻነትን አየር የተነፈሱበት ጊዜም ይህ የ1950ዎቹ አጋማሽና መገባደጃ ነበር። በታሪክ ሊጠቀሱ የሚችሉ የዚያን ዘመን ዓለም አቀፋዊ የለውጥ ክሥተቶች እጅግ በርካታ ናቸው። በእንዲህ ዐይነት ዓለም አቀፋዊ ዐውድ ውስጥ ተገኝ የነበረችው ኢትዮጵያ በጊዜው ምን አስተናገደች? የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ የዚያ ዘመን የለውጥ ትኩሳት የገረመመውን አንድ ወጣት ኢትዮጵያዊ ታሪክና የለውጡን እንቅስቃሴ ሂደት መቃኘት ግድ ይላል።





በ1940ዎቹ አጋማሽና የ1950ዎቹ መጀመሪያ ዓመታት በኢትዮጵያ መሠረታዊ የሆነ ለውጥ እዲመጣ አበክረው ከሚሹ ወጣቶች መካከል አንደኛው ገርማሜ ንዋይ ነበር። ይህ ተራማጅ አመለካከት የነበረው ወጣት የተወለደው በ1916 ዓ.ም. አዲስ አበባ ከተማ ውስጥ፣ ከአራዳ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ከፍ ብሎ በሚገኘው ገዳም ሰፈር ተብሎ በሚጠራው አካባቢ ነው። አባቱ አለቃ ንዋይ የአራዳ ጊዮርጊስ ደብር ካህን ነበሩ። መንዜዋ ወላጅ እናቱ ወ/ሮ ላቀች የዳግማዊ ምኒልክ ሹም የነበሩና የሥራ ብቃታቸውን በታማኝነት ለንጉሡ ያስመሰከሩት የደጃዝማች ገርማሜ ልጅ ነበሩ። በቀዳማዊ `ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥት የንጉሡ ነገሥቱ የክብር ዘብ አዛዥ የነበሩት የብ/ጄኔራል መንግሥቱ ንዋይ የስምንት ዓመት ታናሽ የሆነው ገርማሜ፣ መጠሪያ ስሙን ያገኘው የእናቱ አባት ከሆኑት አያቱ ነው። ይሁን እንጂ በስም ብቻ ሳይሆን በተግባር ሞግሼነት አያቱን መስሎ እንዳደገ የታወቀው እያደር ነው። ገርማሜ አብዛኛውን የአፍላነት ዘመኑን ያሳለፈው ለዕውቀት ከፍተኛ ትኩረት በመስጠት በትምህርት ነው።

ፋሺስት ኢጣሊያ ኢትዮጵያን በወረረበት ዘመን ትምህርቱን ቀጥሎ የነበረው ትንሹ ገርማሜ ከ1933 የአገራዊ ነጻነት ብርሃን ማግስት፣ ወደ ተፈሪ መኮንን ትምህርት ቤት በመዝለቅ የዘመናዊ ዕውቀት ጥሙን ለማርካት ጀመረ። ከተፈሪ መኰንን ወደ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በመዛወርም ቀዳሚ ትምህርቱን አጠናቀቀ። የተማሪዎች ኅብረት መሪነት የመጀመሪያው ዕጣም የወደቀበት በዚሁ ትምህርት ቤት እያለ ነው። ወጣቱ ገርማሜ ወደ አሜሪካ አገር ሄዶ መማር የሚያስችለውን የከፍተኛ ትምህርት ዕድል አገኘ፤ በዚያም ዕድል በመጠቀም የመጀመሪያ ዲግሪውን በፖለቲካ ሳይንስ ከዊስኮንሲን ዩኒቨርሲቲ የተቀበለ ሲሆን፤ ሁለተኛውንና የማስተርስ ዲግሪውን እዚያው አሜሪካ አገር ከሚገኘው ኮሎምቢያ ዩኒቨርሲቲ አግኝቷል።[1]

[1] የመመረቂያ ጽሑፉ ርእስ "በኬንያውያን ላይ የቅኝ ገዦች አስተዳደራዊ መመሪያ ያስከተለው ችግር" በሚል ርእስ እንደ ነበር መረጃዎች ያጠቁማሉ።



ገርማሜ በአሜሪካ ቈይታው የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር ምክትል ፕሬዘዳንት በመሆን ያገለገለ ሲሆን፣ ይህም የወጣትነት ኀሊናው በፖለቲካ ንቃት እንዲዳብር ከፍተኛ አስተዋፅኦ አድርጓል።

ገርማሜ በ1946 ዓ.ም. ወደ ኢትዮጵያ እንደ ተመለሰ፣ በአገር ግዛት ሚኒስቴር መሥሪያ ቤት የሚኒስትሩ የራስ አበበ አረጋይ ጸሐፊ ሆኖ እንዲሠራ ተደረገ። በ1947 ዓ.ም. ራስ አበበ አረጋይን ራስ መስፍን ስለሺ ሲተኳቸው፣ በሚኒስቴሩ መሥሪያ ቤት በጸሐፊነቱ ሥራ ቀጥሎ ነበር። ሆኖም የተቀየሩት አለቃ ለገርማሜ አልተመቹትም። ስለዚህ ከጥቂት ቈይታ በኋላ በ1950 ዓ.ም. ወደ ጡረታ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤት ተዛውሮ ሥራውን ቀጠለ። በዚህ ከመሥሪያ ቤት ወደ መሥሪያ ቤት ዝውውሩም ካያቸው ነገሮች በመነሣት፣ የተማሩ ወጣቶች በየመሥሪያ ቤቱ ተገቢ ስፍራ እንዳልተሰጣቸው በምሬት ይናገር ጀመር። በሠራባቸው ከፍተኛ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ውስጥ ባስተዋለው ባላባታዊ ቢሮክራሲና ሥልጣኔን የሚቃረኑ አሠራሮችም ይበሳጭ ነበር። ከዚህም የተነሣ የንጉሡን የውጪ ፖለቲካ አቅም ባይክድም በአገር ውስጥ ፖለቲካቸው ግን ከፍተኛ ትችት ይሰነዝር ነበር።

ወጣቱ ተራማጅ በጡረታ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤት ለተወሰነ ጊዜ ቢሠራም፣ በመሃል አገር በመሆን ያሳይ የነበረው የማኅበራዊና የፖለቲካ ለውጥ ንቃት ጉምጉምታው በልዩ ልዩ መልኩ ወደ ንጉሡ ዡፋን መድረሱ አልቀረም። ገርማሜን ትንሽ ፈቀቅ ለማድረግ በማሰብም በዘመኑ የኢትዮጵያ ደቡባዊ "ጠቅላይ ግዛት" አካል የሆነው "የወላይታ አውራጃ" ገዥ ሆኖ በንጉሡ ተሾመ። ይሁን እንጂ ይህ የገለልታ አጋጣሚ በፅንሰ ሐሳብ ደረጃ በአእምሮው ለሚጉላሉት የፖለቲካ መፍትሔዎች የቤተ ሙከራ ያህል የጠቀመው ጊዜ ነበር። በወላይታ አውራጃ አጭር



የአስተዳዳሪነት ጊዜው ለምቁን ሕዝቦች በተለይም በገባርነትና በጢሰኝነት ለሚኖሩ የኢትዮጵያ ልጆች የነበረውን ጥልቅ የወገናዊነት ስሜት በተግባር ያንጸባረቀበትና



በእንጻሩም ከንጉሡ ነገሥቱ መንግሥት ከፍተኛ ባለ ሥልጣኖችና የመሬት ከበርቴዎች ጋር ይፋ በሆነ መንገድ ቅራኔ ውስጥ የገባበት ጊዜ ነበር። እንደ ምሳሌ ለመጥቀስም፣ የዕርሻ መሬት ላጡ የአካባቢው ተወላጆች መሬት ማከፋፈሉን በመንቀፍ ከኃይለ ሥላሴ በኩል የቀረበለትን ጥያቄ፡- "ሕዝቡ መሬት ከማጣቱ የተነሣ ጠም አዳሪ መሆኑን በቅርብ ሆኜ በመመልከቴ ለዕርሻ ይሆነዋል ያልኩትን ቦታ ለማከፋፈል ተገድጃለሁ" በማለት በወቅቱ ከእርሱ የሚበልጡ የንጉሡ ሹማምንት ደፍረው ሊተነፍሱት የማይቻላቸውን ምላሽ ሰጥቶበታል።

በወላይታ አውራጃ ገዥነቱ ጊዜ መሬት በመሸንሸንና በማከፋፈል ዝቅ ብሎ ከደኸው ገበሬ ጋር መገናኘት መቻሉ ከገበሬው የወንድማዊነትንና የአባታዊነትን ፍቅር ለማግኘት አስችሎታል። ከዚህ ጋር ተያይዞም በእርሱ የአስተዳዳሪነት ዘመን በአካባቢው የተወለዱ አንዳንድ ልጆችም በእርሱ ስም መጠራታቸው ይነገራል። በኮሎኔል አስናቀ እንግዳ በተጻፈ "ሸክም የማይከብደው ሕዝብ" በተሰኘው መጽሐፍ፤ እንደ ተጠቀሰው "በወላይታ ለሕዝቡ ዘለቄታዊ ጥቅም በሚሰጡ የልማት ተግባራት ላይ ተሳትፎ በሚያደርግበት ሰዓት ቊርስና ምሳውን የሚዘነጋ በመሆኑ፣ ሕዝቡ 'ጾመኛው አገረ ገዥ' የሚል ስም አውጥተውለት ነበር"። ገርማሜ ንዋይ የወላይታ ሶዶ ከተማ ዘመናዊ መልክ እንድትይዝ እንዲሁም የውሃና የመብራት ተጠቃሚ እንድትሆን ማስቻሉ በዚያ አውራጃ ካከናወናቸው ተግባራት መካከል አንዱ ነው። ከዘመን አይሽሬውና ፍትሕ ጉዳይ ከሆነው ጉቦ ጋር ያደረገው ትንንቅም የወላይታ ትግሉ አካል ነበር። ፍትሕ ከጐደለባቸው ግለ ሰቦች ጋር በመተባበርም በልዩ ልዩና አስገራሚ በሆነ ዘዴ ጉቦ የሚቀበሉ ዳኞችን እጅ ከፍንጅ ይይዛቸው እንደ ነበረ በጊዜው የነበሩ ሰዎች ይናገራሉ። በመጨረሻ ከአውራጃ አስተዳዳሪነቱ እንዲነሣ በተደረገ ጊዜም በእጅጉ የተቈጩት እነዚሁ ገበሬዎች ገርማሜን ከነመኪናው በትላልቅ እንጨቶች ረዳትነት በመሸከም በግምት 1 ኪ.ሜ. የሚሆነውን መንገድ ከፍቅር የመነጨ እምባቸውን እያፈሰሱ እንደ ሸኙት ይነገራል።



ከወላይታ አውራጃ አስተዳዳሪነት ቀጥሎ "በቅጣት መልክ" የገርማሜ የሚቀጥለው የግድ ዙረት ወደ ምሥራቅ ኢትዮጵያ ሆነ። የተዛወረውም ወደ ጅጅጋ ነበር።

የገርማሜ ንዋይ ወደ ጅጅጋ መዛወር ምክንያቱ በወላይታ አውራጃ አስተዳዳሪነቱ ቈይታው «እጅግ ነቃ» ተብሎ በመታሰቡ ነው። መቼም የወላይታ ቈይታው በሕዝቡ ዘንድ አስገኝቶለት የነበረውን መወደድ በአዲስ አበባ የነበሩ የሚጠሉት ሰዎች እንኳ አይክዱትም ነበር። እንደ ቀድሞው በጅጅጋ ቆይታውም ነዋሪዎቹ ትምህርት ቤትና የጤና ጣቢያ እንዲቋቋምላቸው፣ ንጹሕ የመጠጥ ውሃም እንዲያገኙ አድርጓል። ከነዋሪው ሕዝብ የሚገኘው የግብር ገቢና በጠረፍ ቀበሌዎች ይካሄድ ከነበረው ንግድ የሚሰበሰበው ቀረጥ ለአካባቢው ኅብረተ ሰብ በሚጠቅሙ የመሠረተ ልማት አውታሮች ማስፋፊያ ላይ እንዲውል ዕቅድ አውጥቶ ተግባራዊ ማድረግም ጀምሮ ነበር።

በጅጅጋ ቈይታው ልክ እንደ ወላይታው ሁሉ ካደረጋቸው የማኅበራዊ ልማት ትግሎች አንደኛው፣ በጊዜው በምዕራብ ጀርመን መንግሥት ተገንብተው በንጉሡ ለኢትዮጵያውያን ሱማሌዎች ለመስጠት ቃል ተገብተው የነበሩት ስምንት ክሊኒኮችና ሐኪም ቤቶች ጉዳይ ነበር። የአገር እድገት ናፋቂው ገርማሜ እነዚህን የጤና አገልግሎት ግንባታዎች እና ሆነው ሲፈራርሱ ስለ ተመለከታቸው፣ ጉዳዩ አሳስቦት ወደ አዲስ አበባ ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር በመሄድ «ለእነዚህ የጤና ማእከላት ተገቢው የመገልገያ መሣሪያና የሰው ኀይል አለመመደቡ ለምን ይሆን?» ብሎ ለጠየቀው ጥያቄ «ከነመኖራቸውም አናውቅም» ተብሎ የተሰጠው መልስ ቢያስደንቀውም «ሕንጻዎቹ ግን በዚያ ስፍራ አሉ» ከማለት በስተቀር ሌላ ምላሽ አልነበረውም።



ይሁን እንጂ በወላይታም ሆነ በጅጅጋ አውራጃዎች እጅግ ደኻ፣ በትምህርት ኋላ ቀርና በወቅቱም ለነበሩት የመሬት ከበርቴዎች ወይም ባለ ርስቶች ገባር የነበረውን ሕዝብ ለማስተማር፣ የአገሩ ሀብት ተጠቃሚ እንዲሆን



ለማስቻልና ሥልጣኑም እንዲሠርጽበት ለማድረግ ያከናውን የነበረው ተግባር ለአንዳንድ የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ሹማምት የሚዋጥላቸው አልነበረም። በይበልጥም የጉቦኛ ዳኞችና እኩይ ባላባቶች ድርጊት እጅግ ተቃራኒና እንቅልፍ ነሺ የነበረው ተራማጅ እንቅስቃሴው ከፍተኛ የሆነ ጥላቻን አተረፈበት። ከዚህም የተነሣ በእርሱ ላይ ለንጉሡ ይቀርብ የነበረው አቤቱታና ክስ ብዙ ነበር። ስለዚህ ልክ እንደ ወላይታው የገኘንት ዘመኑ ሁሉ በጅጅጋም ድኾችን በመቅረብ ለአካባቢው ልማት ያደርግ የነበረው እንቅስቃሴ ስላልተወደደለት ከጅጅጋ እንዲመለስ ተደረገ።

በዚህ ወቅት ሥር የሰደዱ የሥርዓቱን ችግሮች በየዳር አገሩ እየተንከራተቱ ታግሎ መለወጥ የሥልጣኔ ብርሃን ለበራለት ገርማሜ አሰልቺ ቍርጥራጭ ትግሎች ሆኑበት። በየስፍራው ቀዳዳ መጣፍ የትም እንደማያደርስ ተገንዝቦ ለአዲስ ሥርዓት ዕቅድ ልቡናውን አዘጋጀ። ከንጉሡ ጋር ሳይጣላ ሥርዓቱን መለወጥ የማይታሰብ ቢሆንም፣ ሥርዓቱን በግድ ለመለወጥ ግን ከማንም ሰው ጋር፣ ንጉሡንም ጨምሮ ለመጣላት ቍርጥ ውሣኔ አደረገ። ከ"መስከረም 4 ቀን 1953 ዓ.ም." ጀምሮ በዚያው ዓመት በታኅሣሥ ወር የተካሄደውና ሳይሳካ የቀረው የመንግሥት ለውጥ ሙከራ ድርጊት ተፈጻሚ እስከ ሆነበት ጊዜ ድረስ ገርማሜ በአዲስ አበባ ከተማ ቈይቷል።

የኢትዮጵያ በሥልጣኔ ወደ ኋላ መቅረት ይቈጨው የነበረው ገርማሜ ነዋይ፣ በሰሜን አሜሪካ ቈይታው የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር ምክትል ፕሬዝዳንት ከመሆኑ በተጨማሪ፣ በካናዳ ይማሩ የነበሩ የአገሩ ልጆች በአሜሪካ ይገኙ ከነበሩ ወንድሞቻቸው ጋር እንዲቀራረቡ በማድረግ ረገድ ድርሻውን ተወጥቷል። በለውጥ አስፈላጊነት ጉዳይና በተማሩ የኢትዮጵያ ልጆች ብሔራዊ ሚና ላይና በሌሎች ተመሣሣይ ጉዳዮች የሚመክር መድረክ ለመፍጠር ከነበረው ጽኑ ፍላጎት አኳያ በ1948 ዓ.ም. "የቀጨኔ ክበብ" የተሰኘውን የውይይት ኅብረት አቋቁሟል። አገሩን ወደ እድገትና ብልጽግና አቅጣጫ ሊወስድ የሚችለውን የለውጥ ሐሳብ ሊያፈልቅና ሳፈለቀውም ሐሳብ ተግባራዊነት



ቅማቶ የሚሠራ ብሔራዊ ማኅበር ለመመሥረት ያልታከተው ገርማሜ ንዋይ፣ ተራማጅና ለውጥ ፈላጊ አመለካከቱን ከሚደግፉለት አቻዎቹ ጋር ከመምከር ለአፍታም ተዘናግቶና ቦዝኖ አያውቅም ነበር።

ወደ ውጪ አገር ሄዶ መማሩ በሌሎች አገሮች ያለውን ብልጽግናና የፖለቲካ ንቃት እንዲያስተውል ከማድረጉም በላይ፣ ከታዳጊ አገሮችና ከሌሎችም ጭምር ከሚመጡ ተማሪዎች ጋራ የሐሳብ ልውውጥ የሚያደርግበት ዕድል ስለ ሰጠው፣ አገሩ ኢትዮጵያ የሥርዓት ለውጥ እንደሚያስፈልጋት እንዲገነዘብና ለዚህም ለውጥ ማንኛውንም መሥዋዕትነት ለመክፈል እንዲዘጋጅ አድርጎታል። ከዚህም በተጨማሪ በከፍተኛ ደረጃ የተማረው ትምህርት የፖለቲካ ሳይንስ መሆኑና ወደ አገሩም ተመልሶ ለሥራ የተመደበባቸው ቦታዎች በእርከናቸው ከፍ ያሉ በመሆናቸው የሰፊውን ሕዝብ ፍትሕ ማጣት እንዲያይ ረድቶታል። ከዚህም የተነሣ በ"ቀጨኔ ክበበ" እንደዚሁም "በወጣት ወንዶች ክርስቲያናዊ ማኅበር" (ወ.ወ ክ ማ) መድረክ፣ በኢትዮጵያ ዘመናዊውን አስተሳሰብና የሥልጣኔን ፈር የሚያሳይ አመለካከት ይሠርጽ ዘንድ የሚያግባቡ የውይይት ነጥቦች እንዲነሡ ያደርግ ነበር። የገርማሜ የመንግሥት ለውጥ ጥማት ከሌሎች አገሮች የመንግሥት ለውጥ ልምድን የሚጋራ እንዲሆን የግል ጥናቶችም ያደርግ ነበር። ከዚህም በተጨማሪ የወንድሙን የጀነራል መንግሥቱ ነዋይን ከፍ ያለ የሥልጣን ደረጃ ገና ከገሃዱ የለውጥ እንቅስቃሴ በፊት ከለውጥ ፈላጊ ሰዎች ጋር ለሚያደርገው ውይይት ይጠቀምበት እንደ ነበረም ይነገራል።

የገርማሜ ነዋይን ተራማጅ ሐሳብ በመደገፍ ረገድ እነ መንግሥቱ ለማ፣ ስዩም ሰብሐት፣ ኢብራሂም ይመር፣ ገርማሜ ወንዳፍራሽ፣ ዮዲት እምሩ፣ ኃይለ ማርያም ከበደ፣ አምዴ ወንዳፍራሽና ሌሎችም የክብር ዘበኛ መኰንኖች እስከ ታኅሣሥ 1953 ዓ.ም. የለውጥ እንቅስቃሴ መገታት ድረስ ከተራማጁ ወጣት አጠገብ ቆመዋል። ዓላማቸውም፣





"ለኢትዮጵያ ሕዝብ መሪብና መታረዝ፣ ብሎም ለአጠቃላይ ጕስቍልናው ምክንያት የሆነው ችግር መፍትሒ ይፈለግለት፤ ፍትሕ በአገሪቱ ይስፈን! መድልዎ ይወገድ!" የሚሉ ነበር።

ለውጥ ፈላጊነት የሰው ልጅ ዓይነተኛ ባሕርይ መሆኑ ግልጽ ነው። ምንም እንኳ ገርማሜ በግለሰብ ደረጃ የጐደለበት እንዳችም ቍሳዊ ጥቅም ያልነበረው ኢትዮጵያዊ ቢሆንም፣ ለአገሩ አጠቃላይ ብልጽግናን መሻቱና የድኻ ወገኖቹን ወሰን የለሽ ጕስቍልና መመልከቱ፣ የሕዝብ ነጻነትና መብት ተሚጋች እንዲሆን አስገድዶታል። ከንጉሠ ነገሥቱ መንግሥት ባለ ሥልጣኖች መካከል አንዱ ሆኖ በመቀጠል የአገሩንና የወገኑን ጕስቍልና ከማባባስ ይልቅ፦ "ኢትዮጵያንና ሕዝቧን ወደ እድገትና ብልጽግና የሚመራቸው ፈር ቀዳጅ ለውጥ ያሻል" በሚል እምነት፤ ታላቅ ወንድሙን ብ/ጄኔራል መንግሥቱ ንዋይንና ዓላማውን የደገፉትን ሌሎች ኢትዮጵያውያንን በማስተባበር የ1953 ዓ.ም ወርኀ ታኅሣሥ የለውጥ ንቅናቄን መራ። በታሪክ ምሁራን የዐላማ ግልጽነትና የአደረጃጀት ጕድለት እንደ ነበረው የተነገረለት ይህ የለውጥ እንቅስቃሴ ቦምብ በፊውዳላዊው ሥርዐት ላይ በተወረወረ በአሥራ ሦስት ዐመቱ ዳግም ላይከሽፍ መፈንዳቱን ልብ ይሏል።

ይህን በዘልማድ "የታኅሣሥ ግርግር" ተብሎ የሚጠራውን የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሣዊ ሥርዓትን የመሻር ንቅናቄ የመራውና "ለንጉሡ ፍጹም ታማኝ የነበሩትን ጄኔራል መንግሥቱ ንዋይንና ሌ/ኰሎኔል ወርቅነህ ገበየሁን. . . የዐላማው ደጋፊዎች ሆነው በተግባር ከጐኑ እንዲሰለፉ ያደረገ" ወጣቱ ገርማሜ ንዋይ መሆኑን ብዙዎች ያምናሉ። ስለዚህ ሁኔታ ለ50 ዓመታት ያህል (ከቀዳማዊ ኃ/ሥላሴ ሥርዓት ጀምሮ እስከ 1999 ዓ.ም.) የሕግ ጠበቃና አማካሪ ሆነው የሠሩት የ75 ዓመት አዛውንት አቶ ሙሉጌታ በሪሁን የሚከተለውን ይመሠክራሉ፦

እርሱ በዘመኑ ከነበሩት የመንግሥት ባለ ሥልጣናት በአመለካከት የቀደመ ነው። እውነተኛ ፍላጎቱ በኢትዮጵያ ለውጥ ማምጣት



የነበረ መሆኑን የታኅሣሥ 1953 ዓ.ም. ንቅናቄ መሠረትና መደምደሚያ በመሆን አሳይቷል። የግል ብልጽግና መሻትን ጉዳይ ወደ ጐን ብሎ ለድኻው የኢትዮጵያ ሕዝብ ነጻነትና መብት መከበር ሲል፣ በወቅቱ አዲስ ሙሽራ መሆኑን እንኳ ከቁብ ሳይቈጥር ራሱን ለመሥዋዕትነት አቅርቧል። ያለ ገርማሜ ንዋይ የታኅሣሡ ሥርዓትን ለመሻር ያለመ አብዮት የማይታሰብ ነበር። ለቀዳማዊ ኃ/ሥላሴ ፍፁም ታማኝ የነበረውን መንግሥቱ ንዋይንና የደኅንነት ሠራተኛቸው የሆነውን ኮሎኔል ወርቅነህ ገበየሁን ... አመለካከታቸውን በመሞረድ የለወጣቸውና በሕዝባዊ ትግል ውስጥ ወሳኝ የሆነ ሚና እንዲጫወቱ ያስቻለ ... የበሳል አእምሮ ባለቤት የሆነው ገርማሜ ንዋይ መሆኑ የሚያጠራጥር አይደለም።

"የተበላሸው ሥርዓት ከቍንጮው መወገድ አለበት ..." የሚለውን አቋም ይዞ በ36ኛ ዕድሜው መጨረሻ ሕይወቱን እስካጣበት ዕለት ድረስ በተራማጅነቱ የጸናው ገርማሜ ንዋይ፤ ከታኅሣሥ 4 ቀን ምሽት እስከ ታኅሣሥ 5 ቀን ምሽት የዘለቀው የለውጥ ንቅናቄ አልሳካ ካለ በኋላ ... ታኅሣሥ 15 ቀን 1953 ዓ.ም. ከቀኑ 10 ሰዓት አካባቢ ዝቋላ አቅራቢያ በምትገኘው "ድሬ ጨለባ" በተባለው ስፍራ ራሱን አጥፍቷል። እንዲህ ከመሆኑ ጥቂት ቀናት በፊት ግን በጊዜው አገሪቱ ለእንደዚያ ያለ ድንገታዊ ለውጥ አልተዘጋጀችም ነበረ ብለው የሚያምኑትና የወንድማማቾቹ የቅርብ ወዳጅ እንደ ነበሩ የሚናገሩት ዶናልድ ኤን ሌቪን የገርማሜን አንድ የመጨረሻ የስንብት ቃል ፦ «ብንሸነፍም ብንሞትም እንኳ በዚህች ሐሰት በበዛባት ምድር ቢያንስ ቢያንስ ቅንጣት እውነት ይነገር ዘንድ እባክህ ታሪካችንን ለዐለም ሁሉ ንገርልን» ያላቸውን ሰምተው ነበር። ይህን ከነገራቸው ጥቂት ወራት በኋላ የገርማሜን አደራ በመጠበቅ እንዲት መጣጥፍ ቢጽፉ ንጉሡ ተቀይመዋቸው ኖሮ የአሜሪካንን መንግሥት እሰርልኝ ብለው ጠይቀው ነበር፤

ነገር ግን ሊሆን አልቻለም።



ገርማሜ ንዋይ ታኅሣሥ 17 ቀን አስከሬኑ በምኒልክ አደባባይ የተሰቀለ ሲሆን፣



ታላቅ ወንድሙን ብ/ጀኔራል መንግሥቱ ንዋይን ለመግደል ሙከራ ማድረጉና ከዚህም ሙከራ በኋላ ራሱን ያጠፋ ስለ መሆኑ የጽሑፍ መረጃዎች ያስረዳሉ።

**በነ አገራዊ ለውጥ የተጠሙት የወንድማማቹ ነፍሶች፣ በልጅነታቸው ከመንደራቸው ቍልቍል ወርደው ይጫወቱበት በነበረው የጊዮርጊስ ፈፋ ላይ «የወንበዴን» ሞት በስቅላት ገመድ አስተናገዱት። የለውጡ ፍላጎት ሳያበቃ እነርሱ አበቁ።**



## መወድስ

**ዘጠኝ ወር ሲሞላው ጽንሱ ራሱ ገፍቶ**
**ውስጣዊ ውጫዊ ሁኔታ ተሟልቶ**
**የሕዝቡ ሕሊና ንቃቱ ጎልብቶ**
**ለውጥ ይወለድ እንጂ አይጨንግፍ ከቶ**
**በጣሙን ይቆጫል ገርማሜ ወጣቱ**
**ባጭር መቀጨቱ ሳይደርስ ሰዓቱ**

## ትምህርተ ውልብታ

የገርማሜ ታሪክ ፣ ምሑርነት በማኅበረ ሰብ መዋቅር ሽቅብ እየመጠቁ ከድኻው የሚራራቁበት መሰላል ሳይሆን ፣ አንድ ሰው እውቀት በለገሰው ብርሃን የደኸውን ችግር አይቶ ሊቀርፍለት ወደ እርሱ የሚጓዝበት የትሕትና መንገድ መሆኑን በሚገባ ያስተምራል።

ለውጥ አራማጅ መሆን የሕይወት መሥዋዕትነትን ይጠይቃል።





## የውልብታ ምንጮች


Remarks by Donald N. Levine on *the Occasion of the Award of Honorary Doctorate to himself, by Addis Ababa University,* July 24, 2004

R Greenfield, *Ethiopia,* London 1965 p 372-373

Christopher Clapham *Imperial Leadership in Ethiopia, African Affairs,* Vol. 68, No. 271 (Apr., 1969), pp. 110-120 this article consists of 11 page(s).

ባሕሩ ዘውዴ የኢትዮጵያ ታሪክ ከ1848 እስከ 1966 ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕሬስ 1989 ዓ.ም.

ፋንታሁን እንግዳ በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ አስተዳደር ጎልተው የወጡ ፖለቲካዊ ችግሮችና ትግሎች በቅርብ ባለሟላቸው የሕይወት ታሪክ መነሻነት ሲገመገሙ አዲስ አበባ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት 1997 ዓ ም

ይሁን ዓለም ሰገድ "ፋና ወጊ" ነሐሴ ወር 1984 ዓ.ም.

ቃለ ክርስቶስ ዓባይ ኮሎኔል፣ "የ1953 የመንግሥት ግልበጣ ሙከራና ከ1908-1966 ዓ.ም. የኢትዮጵያ ታሪካዊና ፖለቲካዊ ሂደት" 1997 ዓ.ም.

ማለዳ መጽሔት መጋቢት 1985 ዓ.ም. ቁጥር 3

ጦቢያ መጽሔት ጥቅምት 1989 ዓ.ም.

ከጋዜጠኛ ማዕረጉ በዛብህ ጋር ግንቦት 14 ቀን 99 ዓ.ም. የተደረገ ቃለ ምልልስ።

ከአቶ ሙሉጌታ በሪሁን (የሕግ አማካሪና ጠበቃ) ጋር ረቡዕ ግንቦት 15 ቀን 1999 ዓ.ም. የተካሄደ ቃለ ምልልስ።




አቶ ማዕረጉ በዛብህ፡- በ1970ዎቹ መጨረሻ በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የኢትዮጵያ ቋሚ መልዕክተኛ ጽ/ቤት የፕሬስ አማካሪና በቀዳማዊ ኃ/ሥላሴ ዘመን ማክተሚያ ግድም የቢቢሲ ዘጋቢ የነበሩ። "የሕዝብ ለሕዝብ ኢትዮጵያ" የኪነት ቡድን የሕዝብ ግንኙነት ኃላፊ በመሆን የሠሩ። የአዲስ ዘመንና የዛሬይቱ ኢትዮጵያ ጋዜጣ አዘጋጅ ሆነው ያገለገሉና በአሁኑ ወቅት "በዩኒቲ ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ" የጋዜጠኝነት መምህር።

ኮሎኔል አስናቀ እንግዳ በእነገርማሜ ንዋይ ዘመንና ከዛም በኋላ በነበረው ጊዜ ለውጥ ፈላጊ መኮንን የነበሩ፣ አሁን በአሜሪካ ነዋሪና "ሽክም የማይከብደው ሕዝብ" መጽሐፍ ደራሲ።

አቶ ሙሉጌታ በሪሁን፡- ለ50 ዓመታት ያህል (ከቀዳማዊ ኃ/ሥላሴ ሥርዓት ጀምሮ እስከ 1999 ዓ.ም.) የሕግ ጠበቃና አማካሪ ሆነው የሠሩ የ75 ዓመት አዛውንት።





# የአንባቢው የግል ማስታወሻ










# ፲፫



ቄስ ጉዲና ቱምሳ

1921– 1971

ፍትሕና እውነትን ለመታደግ የተከፈለ መሥዋዕትነት

## ስለ አለማመን ተገቢ የሆነው ምስክርነት በእምነት መኖር ነው

"ከእናንተ ውስጥ ማናችሁም ቀኔ ደርሶ ሕይወቴ ስታልፍ የተገኛችሁ እንደ ሆነ የቀብሬ ሥነ ሥርዐት ረጅም እንዳይሆን መፈለጌን እንድታውቁልኝ፤ ስለ ሕይወት ታሪኬ የሚናገር ሰው ካገኛችሁ ሀጠር እንዲያደርገው ንገሩት፣ የኖቤልን ሽልማት ስለ ማግኘቴ እንዳይናገሩ ንገሯቸው፣ እስከዚህም አስፈላጊ አይደለም። ሦስት መቶና አራት መቶ የሚሆኑ ልዩ ልዩ ሽልማቶችም እንዳሉኝ መጥቀስ አያስፈልግም። ቁም ነገር አይደሉምና። የት የት እንደተማርሁም እንዳይናገሩ ንገሯቸው። ከመካከላችሁ አንዱ ማርቲን ሉተርኪንግ ጁኒየር ሌሎችን ለማገልገል ሕይወቱን የሰጠበትን ቀን ትውስ እና ትዝ እንዲለው እሻለሁ። ማርቲን ሉተር ኪንግ ጁኒየር ማንንም ለማፍቀርና ለመውደድ ይጥር የነበረበትን ቀን ከመካከላችሁ አንዱ እንዲያስታውሳት እወዳለሁ። ስለ ጦርነቱ ባለኝ እምነት ትክክለኛነቱን በማስታወስ የተናገርሁበት ቀን ትውስ ቢላችሁ ደስ ይለኛል። የተራቡትን ለማብላት የሞከርሁበትን ቀን እንድታስታውሱ ከመመኘቴም በላይ እስር ቤት የሚገኙትን ለማጽናናት የጠየቅሁበትን ቀን እንድታስታውሱ እፈልጋለሁ። የሰውን ልጅ የሚወድና ሰውን ለማገልገል የተፈጠረ ነው እንድትሉ እሻለሁ።"

ማርቲን ሉተር ኪንግ ጁኒየር፣ የካቲት 4፣ 1964።

ማርቲን ሉተር ኪንግ በኢ-ፍትሐውያን ጥይት ሕይወቱ ከማለፉ ቀደም ባሉት ዓመታት፣ በመላው አሜሪካ ያጋመው ሀመፅ አልባ የነጻነት ትግል ምድራቱን ያነቃበትና በተለይም ጥቍሮችን ያተጋበት ጊዜ እንደ ነበር የሚዘነጋ አይደለም። ታዲያ በምድረ አሜሪካ የሚኖሩ እኒያ ጥቍር የአገራቱ ግፉአን፣ ለፍትሕና ለእውነት የከፈሉት ኪዳናዊ ፍልሚያ ቀልባቸውን የጠለፈው ኢትዮጵያዊው ቄስ ጉዲና ቱምሳ የነጻነቱ ትግል ሽቅብ ወጥቶ በጋመበት ወቅት ለከፍተኛ ትምህርት ሰሜን አሜሪካ ዘልቀው ኖሮ፣ አብነታዊ ፈለግ ያለው የኪንግ ፋና ቀደም ሲል በውስጣቸው ለተቀጣጠለው የሐቅ ቀንዲል ተጨማሪ ዘይት ለግሶታል።



እኒህን ሰው ከማርቲን ሉተር ጋር የሚያመሳስላቸው ብዙ ነገር አለ፤ የትውልድ ዘመን ጓደኛ (Contemporary) ከመሆናቸው ሌላ ሁለቱም የጨቋኝ ሥርዐት ትግል ሰለባ ናቸው።



እነዚህ ሁለት ሰዎች ትውልዳቸው በተለያዩ ሁለት አህጉራት ቢሆንም እንኳ፣ ሁለቱም በኖሩባቸው አገሮች ማኅበራዊና ፖለቲካዊ ኢፍትሐዊነትን በግልጽና በሚያስከፍለው ዋጋ የተቃወሙ የቤተ ክርስቲያን ካህናት ነበሩ። ከአሜሪካ መልስ በኖሩበት ሀጭር የሕይወት ዘመን ለእውነት፣ ለፍትሕና ለእኩልነት ከመሟገት አንድ ጊዜም ፊታቸውን አዙረው አያውቁም።

ቄስ ጉዲና ቱምሳ በ1921 ዓ.ም. በባሬዋ ምዕራብ ወለጋ በጂ በተባለ ሥፍራ ተወለዱ። ሀሥር ዓመት ሲሞላቸው ወደ ት/ቤት መሄድ የጀመሩት ቄስ ጉዲና ከጥቂት የት/ቤት ቈይታ በኋላ፣ የ "qaallu" ን መንገድ አምርረው በመቃወማቸውና የአካባቢውን አድባር ዛፍ በማስወገዳቸው ወላጆቻቸው ከቤት አስወጧቸው። ከዚህ የተነሣ እግር ወደ መራቸው ወደ ነጆ ነጐዱ፤ እድላቸው ሠምሮ ነጆ የሚገኘው የሚስዮን ትምህርት ቤት በዐዳሪነት ገብተው እንዲማሩ ፈቀዱላቸው።

ከሁለት ዓመት በኋላ ለተከታዩ ትምህርት ወደ ነቀምቴ መጓዛቸው ግድ ሆነ። ይሁን እንጂ በአድባሯ ዛፍ ሳቢያ ከቤት ከወጡ ወዲህ ከወላጆቻቸው አንዳች ድጋፍ ስላልነበራቸው መራር ዓመታትን አሳልፈዋል። ነቀምቴ እያሉ የአባታቸውን ዜና ዕረፍት ሰሙ። በዚያን ጊዜ ራሳቸውን የሚደግፉበት ሥራ አግኝተው ስለ ነበር ወንድሞቻቸውና እኅቶቻቸውን ሜዳ ላይ ያለ አባት ተበትነው ማየት ስላልፈለጉ እኅቶቻቸውንና ሁለት ወንድሞቻቸውን ወደ ነቀምቴ በማምጣት ይረዱ ጀመር።

ቄስ ጉዲና በሌላ ሙያ ለመሰማራት ትምህርታቸውን ያቋረጡት ወደ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ሳይዘልቁ ነበር። ሆኖም ብልኅነታቸውን ያየ አንድ የውጪ አገር ዜጋ ወደ አሜሪካ በመሄድ ኰሌጅ ገብተው እንዲማሩ ያቀረቡት ሐሳብ፣ ከትምህርታቸው አለመግፋት የተነሣ በዩኒቨርሲቲው ተቃውሞ ገጠመው። ይሁንና ሰውየው፣ "እስቲ እዩአቸው" በማለታቸው፣ በዚህ ሐሳብ የተስማማው ዩኒቨርስቲ ወጣቱን ጉዲናን ተቀበላቸው። በቅርብ የሚያውቋቸው አንድ ወዳጃቸው፣ "የሁለት ሰው አእምሮ ይዟል" ብለው የመሰከሩላቸውና ከልጅነታቸው ጀምሮ



ብሩህ አእምሮን እንደ ታደሉ የሚነገርላቸው ቄስ ጉዲና የተገኙት እውነትም እንደ ተባለላቸው ሆነው ነበር። በ Lutheran North Western Theological Seminary, U.S.A. የሚሰጠውን ትምህርት በዐጭር ጊዜ በብቃት አጠናቀቁ።

የሥራ ባልደረቦቻቸው፣ በወዳጅነት የሚቀርቧቸውና በልዩ ልዩ ሥራዎቻቸው ከሩቅም ሆነ ከቅርብ የሚያውቋቸው ሁሉ የቄስ ጉዲናን የአእምሮ ብሩህነት፣ እርቆ አሳቢነትና ብሎም ድንቅ አመራር ሳያወሱ አያልፉም። በተለይም በአዲስ አስተሳሰብ ብቅ ያሉበትና የበርካታ ሰዎችን ትኩረት የሳቡበትን፣ «ወንጌልን በማወጅና በሰው ልጅ እድገት መካከል ያለው ተቀባባይ ግንኙነት» "On The Interrelation of Proclamation of The Gospel and Human Development." የተሰኘውን ሥራቸውን መጥቀሱ አግባብ ይሆናል። ከዚህም ሌላ፣ «የክርስቲያን ማኅበራዊ ሱታፌ ሚና» "The Role of Christians in a Given Society" የተባለው ጥናታዊ ጽሑፋቸው የታየው እንደ አቅጣጫ አመላካች ሆኖ ነው።

በ1964 ዓ.ም. በደቡብ አፍሪካ ያለችው ቤተ ክርስቲያን የቱን ያህል የአፓርታይድ ተጽዕኖ ዐርፎባታል የሚለውን ርእሰ ጉዳይ ለማጥናት ከሌሎች ስድስት ነፍሶች ጋር 'World Lutheran Federation"ን በመወከል ወደዚያ አቀኑ። የደቡብ አፍሪካው ጉዞ ሲታቀድ የፕሪቶሪያ መንግሥት በቀለማቸው ሳቢያ ወደ አገር እንዳይገቡ ቪዛ የከለከላቸው ቢሆንም፣ የልዑካን ቡድኑ እርሳቸው ካልተካተቱ ጉዞውን እንደሚሰርዝ በገለጸው መሠረት ከፕሪቶሪያ መንግሥት ይለፍ ተሰጣቸው። ለዚህ ችግር መፍትሔ ለማስገኘት ሲባል በወቅቱ በተፈጠረው ንትርክ ምክንያት ቡድኑ ወደ ደቡብ አፍሪካ መድረስ ከሚገባው ቀን አንድ ወር ያህል ዘግይቷል።



ቄስ ጉዲናን የመጀመሪያው የዘረኝነት ወላፈን የገረመማቸው የልኡካን ቡድኑ ወደ ጆሃንስበርግ እንደ ደረሰ ነበር ። በአየር ማረፊያው የነበረው ምግብ ቤት የቀለም



ልዩነትን ያደርጋል። ከባሕርያቸው አድልዎአዊውን አካሔድ አጥብቆ ተቃዋሚ የነበሩት እኒህ ቄስ፣ "እሻፈረኝ!" በማለት በቀጥታ ወደ ነጮቹ ምግብ ቤት በማምራት ወንበር ስበው ተቀመጡ። የታዘባቸው አስተናጋጅ ግን አልነበረም። በዚህም በአገሪቱ ውስጥ ያለው የዘረኝነት መርግ የቱን ያህል ከባድ እንደ ሆነ ተገንዝበዋል።

ከአውሮፕላን ማረፊያ እንደ ወጡ ሆቴል ማግኘት ነበረባቸውና ዐብሯቸው ያለው ቡድን ወደ ተዘጋጀለት ማረፊያ እንዲያመራ ሲነገረው፣ ብቻቸውን የተተውት ቄስ ጉዲና ከቶም ይህን ግፍ ሊሸከም የማይችል ኅሊናቸው የተቃውሞ ድምፁን አሰማ። "እሻፈረኝ!" በማለት ተቃወሙ። ይህን ያዩ አንድ ነጭ የደቡብ አፍሪካ ቤተ ክርስቲያን ካህን ጆሃንስበርግን እስኪለቁ ድረስ ወደ ቤታቸው በመውሰድ ማረፊያ ሰጧቸው።

ቀጥሎ በሂዱበት የደርባን ከተማም ይኸው የዘረኝነት ችግር ቀድሞ ጠበቃቸው። ይሁን እንጂ እዚያም ቢሆን ተቃውሞአቸውን ከማሰማት አላፈገፈጉም። ከዚህ የተነሣም የሚሰጣቸውን የሆቴል መስተንግዶና የዕለት ቀለባቸውን ላለመውሰድ ቍርጥ አቋም ወሰዱ። ቡድኑ ደርባንን ለመልቀቅ ታክሲ መከራየት ያስፈለገው በዚህ ጊዜ ነበር ። የታክሲው ሾፌር ከነጮቹ ጋር መሳፈራቸው የማይቀር መሆኑን ሲያይ፣ <<ጥቍር አላሳፍርም>> አለ። ጓደኞቻቸው ኢትዮጵያዊ መሆናቸውን ቢያስረዱም ፈጽሞ ሊቀበላቸው ፈቃደኛ አልሆነም። የገጠመውን ሁኔታ ወደ ትራንስፖርት ካምፓኒው ደውሎ ሲያስረዳ ሥራ አስኪያጁ፣ <<ዲቃላ ነው ወይስ ጥቍር>> ሲል ጠየቀ፤ <<ይህ ሁሉ ከሆነ በኋላ ግን መጨረሻ ላይ ሊያሳፍሩኝ ስምምነት ላይ ተደረሰ>> ይላሉ ቄስ ጉዲና።

በደቡብ አፍሪካ ስላደረጉት ጥናታዊ ጉብኝት የተጻፈ ማጠቃለያ ሰነድ ቤተ ክርስቲያን በማኅበረ ሰቡ ውስጥ ያላትን ሚና የሚያመለክት ሲሆን፣ ሰነዱ ደቡብ አፍሪካ የቱንም ያህል ሀብታም አገር ብትሆንም፣ የተገፉ



ቀቀር ነዋሪዎቿ እንደ ሰው እንደማይታዩና እንዳችም ዕድል እንደሌላቸው በማስገንዘብ በቤተ ክርስቲያን በኩል የውጪም ሆነ የአገር ውስጥ ትምህርት እንዲያገኙ ማኅበራዊ እድገታቸው ላይ ትኩረት እንዲደረግ፣ የመድኃኒት አቅርቦት ከፍ እንዲልላቸው፣ የሙያና የቀለም ት/ቤቶችም እንዲከፈቱላቸው የሚያሳስብ ነው። ቄስ ጉዲና በደቡብ አፍሪካ ያደረጉትን ቄይታ አጠናቀው ወደ ኢትዮጵያ ሲመለሱ ከኢትዮጵያን ሄራልድ ጋዜጣ በተደረገላቸው ቃለ መጠይቅ፣ <<በደቡብ አፍሪካ ያየሁትን ዘረኝነት ከገመትሁት በላይ አስከፊ ሆኖ አግኝቼዋለሁ>> ሲሉ ተናግረዋል።

ቄስ ጉዲና፣ ይልቁንም የኮሚኒዝም ሥርዐት በኢትዮጵያ ውስጥ ከመታየቱ አስቀድሞ ከኋላው ዐዝሎ የሚመጣው የክሂዶተ ፈጣሪ ፍልስፍና፣ ከራሱ ምንጭ የፈለቀ ሳይሆን ከእርሱ በፊት ባሉት የተለያዩ ንጽረታት ውስጥ የተከሠተ መሆኑን፣በተለይም "አለማመን በአንድ የፖለቲካና የሶሻል ሥርዐት ብቻ አይወሰንም" በሚለው አባባላቸው ማርክሲዝምን ከልዩ ልዩ ፍልስፍናዎች አንጻር እየተነተኑ በማስረዳት ሊወሰድ የሚገባውን ርምጃ ቀደም ብለው አመላክተዋል።

> *"አለማመን ሲሰማ ወይንም ሲስፋፋ ስናይ መልሳችን ሁኔታውን መጨቄን (መግታት) ሊሆን አይችልም። እኛ ክርስቲያኖች የማመን መብታችንና ማመን እንዲስፋፋ ያለን ምኞት እንዲከበር ከፈለግን፣ የማያምኑ ሰዎችንና ሊያምኑ የማይችሉ ሰዎችንም መብት ማክበር አለብን። ሌላ አስተያየት ያላቸውን ሰዎች መጨቄን (መግታት) እነርሱን የማሳመን መንገድ አይደለም። ነገር ግን ማመናችንንና እምነታችንን መቀጠል አለብን። በዓለም ተስፋ ለሌላቸውና ያለ አምላክ ለሚኖሩ፣ በግብዝነትና በትዕቢት ሳይሆን፣ 'በእናንተ ስላለ ተስፋ ምክንያት ለሚጠይቋችሁ ሁሉ መልስ ለመስጠት ዘወትር የተዘጋጃችሁ ሁኑ፣ ነገር ግን በየዋህነትና በፍርሀት ይሁን።' ተብሎ እንደ ተጻፈ መሆን አለበት" ሲሉ ጽኑ እምነታቸውን አሳውቀዋል።*






ደግሞም ፣«ስለ አለማመን ተገቢ የሆነው ምስክርነት በእምነት መኖር ነው።» በሚለው ጽሑፍ መርሆአቸው የሚታወሱት እኒህ ቄስ፣ ነገሮችን ከአንድ አንጻር ብቻ እያጠነጠኑ ለሌሎች ሁነቶች በርን ዝግ ማድረግም አግባብ እንዳልሆነ በተከታዩ መሥመር እንዲህ ሲሉ ያስገነዝባሉ፤ <<ሰውንና ዓለምን በግልጽነት እንድናውቅ ከእኛ ይጠበቃል። ዓለም በትኩሳ የተሠራ የአቶሞች ክምችት፣ ወይም የተዘጋ ነገር አይደለም። ሰው ቍስ አካል ብቻ አይደለም። ንቃተ ኅሊናና ስሜት ብቻ ያለውም አይደለም። በእግዚአብሔር መልክ ተፈጥሯል። ሰዎች ነጻነት፣ አንድ ነገር ፈጥሮ የመሥራት ችሎታ ክብርም አላቸው። ይህን ያገኙት ደግሞ ከእግዚአብሔር መልክ ነበር። ስለ ዓለምና ስለ ማቴሪያሊስት የተዘጋ ዕውቀት መያዝ ለሳይንስና ለተፈጥሮ በጣም አስፈላጊ የሆኑትን አንዳንድ ነገሮች መካድ ይሆናል።>> በማለት ለአማኒው ማኅበረ ሰብ ምክንያታዊነትን ማስተናገድ ብልኀነት እንደ ሆነ አስገንዝበዋል።

የሐሳቦችንና የድርጊቶችን አካሄድ እንዲህ እየፈረጁ ያስቀመጡና እንደ ባለ አእምሮ መቀበል የሚገባንን ሁነቶች ያመላከቱን ቢሆንም፣ ከማርክሲዝም ንጽረተ ዐለም አኳያ ግን በተለይ ክርስቲያኑ ማኅበረ ሰብ ግብዝነት በሌለበት የእምነት መድረክ ላይ በቈራጥነት የመራመድ ዐቢይ ተልእኮ ያለው መሆኑን በኮሚኒስታዊው መንግሥት ዋዜማ ላይ ተናግረዋል። ጌርድ ዴኬ የተባለ ጸሐፊ፣<<The role of Gudina Tumsa in a critical dialogue between Marxism/ Socialism and Christianity" በተሰኘ ጽሑፉ፣ ቄስ ጉዲና እንደ ኢትዮጵያውያን ዘመን አቈጣጠር በ1967 ዓ.ም. በዚህ ጉዳይ ላይ የተናገሩትን ኀይለ ቃል እንዲህ ሲል አስፍሮታል፦

> *<<ቤተ ክርስቲያን በምታምነው እውነትና በቍስ አካልነት መካከል አንዳች ማመቻመችም ሆነ ዕርቅ ሊኖር እንደማይገባ ግልጽ መሆን አለበት። ከዚህም የተነሣ ቤተ ክርስቲያንና የማርክሲዝም ፍልስፍና ከቶም ዐብረው መኳዝ የሚችሉበት ፈለግ የላቸውም። የማቴርያሊዝም አስተሳሰብና የኑሮ ዘይቤ ከሚጨበጥ አሳብ ጋር ብቻ የተጐዳኘ፣ ከቍስ*



*የፈለቀ ሲሆን፣ የቤተ ክርስቲያን ሀልውና ግን ከላይ ከመጣው ከእግዚአብሔር መንፈስ ጋር የሚገኝ ነው።"*

በብዙኃኑ አእምሮ ውስጥ፣ "ፈጽሞ ሊሄድበት አይቻልም።" በተባለ ሁኔታ ላይ በመራመድ ውጤት የማምጣት ጉዳይ ለቄስ ጉዲና የጸጋ ያህል ይቈጠራል ቢባል ማጋነን አይሆንም። <<የኢትዮጵያ አብያተ ክርስቲያናት መተባበር ጉባኤ>> የተሰኘው ራእይ ከዚህ የ<<አይቻልም>> ተግባራት መካከል ተፈርጆ በኋላ ግን ወደ እውነታ ከመጡት መካከል ሊመደብ ይችላል።

ይህ በኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ አብያተ ክርስቲያናት (የኢትዮጵያ ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት፣ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንና የኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያንን ጨምሮ) በጋራ በሆኑ ጉዳዮቻቸው ላይ በብረው የመሥራትን ራእይ ፀንሶ የተነሣው ጉባኤ በቄስ ጉዲና ያላሰለሰ ጥረት ሀልውና ያገኘ ቢሆንም፣ ለኅልፈተ ሕይወታቸው ምክንያት ከሆኑት ነገሮች አንደኛው ሳይሆን አይቀርም። የመተባበር ጉባኤው መስከረም 1969 ዓ.ም. ሲመሠረት፣ ከመንግሥት ዕውቅና የጠየቀው ግን በ1971 ዓ.ም. እንደ ነበር ሰነዶች ያወሳሉ። በመተባበር ጉባኤው ውስጥ የነበሩት አንዳንድ የሃይማኖት ድርጅት ተወካዮች እንደሚናገሩት ከሆነ ይህ የ፣«ዕውቅና ስጡን» ጥያቄ ለመንግሥት የሚዋጥለት ሆኖ አልተገኘም።

በወቅቱ በርካታ የውጭ መገናኛ ብዙኃን በኢትዮጵያ ውስጥ የሃይማኖት ነጻነት እንደሌለ አማኞችም እየታሠሩ፣ እየተሠቃዩና እየተገደሉ እንዳሉ ቢዘግቡም፣ መንግሥት ይህን ዘገባ ለማስተባበል ከፍተኛ ጥረትና ሙከራ አድርጓል። በ1970 ዓ.ም. ሁኔታውን እንዲመረምር በመንግሥት የተሰየመው ኮሚቴ የተለያዩ የአገር ውስጥና የውጪ አገራት የሃይማኖት ድርጅት ተወካዮች በተገኙበት በአፍሪካ አዳራሽ አንድ ስብሰባ ጠራ። በስፍራው የመተባበር ጉባኤው አባላትም ተገኝተዋል።




ስብሰባው፣ የተለያዩ ጥናታዊ ጽሑፎች



የቀረቡበት፣ አካሄዱም መንግሥት በቀደደለት ቦይ የፈሰሰ ቢሆንም በመጨረሻው ተናጋሪ በቄስ ጉዲና ቱምሳ ንግግር ግን ብርቱ የሆነ ተግዳሮት ጠበቀው። ቄሱ በጉባኤው ላይ የተነገረው ቅጥፈት ሁሉ እንዳሳዘናቸው ከገለጡ በኋላ በኢትዮጵያ ውስጥ እርሳቸው እስከሚያውቁት ድረስ የሃይማኖት መረገጥና የምእመናን ሥቃይ እያየለ መምጣቱን ስፍራና ቦታ ጠቅሰው የተፈጸመውንም ግፍ ሁሉ እየዘረዘሩ ባስቀመጡት መረጃ ሐቁን አወጡ። የስብሰባው አካሄድ ከታለመለት ፈር እያፈነገጠ መምጣቱ ያስደነገጠው ደርግ ሁኔታዎችን በማረጋጋት ጉባኤውን የበተነ ቢሆንም፣ ቄስ ጉዲናን ግን በመንጋጋው ለማድቀቅ ጥርስ ውስጥ አስገባቸው።

ለኅትመት ባልበቃው የህብታሙ ቡላ ሥራ ውስጥ የተካተተው አንድ ጽሑፍ እንደሚያብራራው፣ ጥቅምት 1971 ዓ.ም. የመንግሥት አካላት ቄስ ጉዲናን በመጥራት፣ አብዮቱን መቃወማቸውንና ተቃዋሚ የፖለቲካ እንቅስቃሴም የሚደግፉ መሆናቸውን ከገለጠላቸው በኋላ፣ ያም ሆኖ ከመንግሥት ጋር የሚተባበሩ ከሆነ አንድ ዓለም ዐቀፍ ኀላፊነት ሊሰጣቸው እንደሚችል በመግለጽ ቢያባብላቸውም፣ ቄስ ጉዲና ግን ፈጽሞ አልተስማሙም።

ባለቤታቸው ወ/ሮ ፀሐይ እንደሚያስታውሱት፣ ወታደራዊው መንግሥት፣ <<ከአገር ውጪ ሄደህ ገንዘብ ጠይቅልን>> በማለት ሊያግባቧቸው ቢሞክሩም፣ ከጽኑዕ መሥመራቸው የተነሣ ሊሳካለት እንዳልቻለ ይናገራሉ። በአንድ ወቅት ለሴት ልጃቸው በጻፉት ደብዳቤ፣ <<ከዚህ የሰውን መብት በሰፊው ከሚረግጥ መንግሥት ጋር ከመሥራት ሞት ይሻለኛል>> በማለት አቋማቸውን ገልጠውላታል።

ሐምሌ 21 ቀን 1971 ዓ.ም. በሥራ ተወጥረው ዋሉ። ምሽት ላይ በካዛንቺዝ አካባቢ በሚገኘው ዑራኤል መካነ ኢየሱስ የወንጌል ስብከትና አስተድዋምም በዚያ ቦታ ሌሎች ተግባራትን ያከናውኑ ስለ ነበር ዕረፍት አልነበራቸውም።



በዕለቱ የሆነውን ሁሉ ሴት ልጃቸው ሌንሴ እንዲህ ስትል ትገልጻለች፤<<በዕለቱ ሊሰብክበት የተዘጋጀበትን የወንጌል ክፍል ካነበበ በኋላ፣ 'ዳግመኛ የሚያስሩኝ ይመስልሻል?' ሲል ጠየቀኝ፣ <ፈጽሞ!> ሁለተኛ ወደ እስር ቤት አይመልሱህም በማለት መለስሁ፤ እርሱም፣<አየሽ፣ ከዚህ ቀደም በሰበክሁበት ክፍል ላይ ነው ዛሬ ማታ የምናገረው።>> አለኝና ወደ ተግባሩ ሄደ። የወንጌል መልእክት አሰምተው ከቤተ ክርስቲያን ከወጡ በኋላ የተከሠተውን ሁኔታ ደግሞ ባለቤታቸው ወ/ሮ ፀሓይ እንዲህ በማለት ይገልጡታል፡-

<<ከስብሰባው በኋላ ወደ ቤታችን ለመሄድ መኪናችን ውስጥ ገባን። ከዚያም ወደ ዋናው ጐዳና የሚያመራውን መንገድ እንደ ያዝን የፖሊስ መኪኖችና በርካታ የወታደር ጂፖች መንገዱን ዘግተውት አየን። ከኋላችን ሁለት ተሽከርካሪዎች ተከትለውናል። ወደፊት ለመሄድም ሆነ ወደ ኋላ ለመመለስ አልተቻለንም። እንድንቆም አዘዙን። ከመኪናው የኋላ ወንበር የተቀመጠችውንና ዐብሩን የነበረችውን አንዲት ሴት ጐትተው አወጧት። ከዚያም ቦርሳዬንና ከመኪናው ውስጥ ያገኙትን ሁሉ ወሰዱ። ወደ ሌላ መኪና እንድገባ ካስገደዱኝ በኋላ ባለቤቴንም ሌላ ተሽከርካሪ ውስጥ ገፍተው አስገቡት። ከዚያ ጊዜ በኋላ ጉዲናን አላየሁትም።>>

ወ/ሮ ፀሓይን የያዘችው መኪና ወደ ደብረ ዘይት መሥመር ከነፈች። በመጨረሻም በአውላላ ሜዳ ላይ ከመኪና እንዲወርዱ አዘዟቸው። ሰዓቱ የመሸ በመሆኑ ወ/ሮ ፀሓይ የት እንዳሉ አላወቁም፤ <<. . ከወዲያ ወዲህ ተቅበዘበዝሁ በመጨረሻም አንድ የነዳጅ ማደያ ስፍራ እንደ ደረስሁ፣ ሠራተኞቹ በከተማ አውቶቡስ ወደ ቤቴ የምደርስበትን 0.15 ሣንቲም እንዲሰጡኝ ጠየቅኋቸው። የነዳጅ ማደያው ባለቤት እንዲያ ሆኜ ሲያየኝ፣ 'ምነው? ምን ነካሽ?' ሲል ጠየቀኝ፤ አሁን ልናገር አልችልም>> ስል መለስሁ። አንድ ብር ሰጠኝ። ቤት እንደ ደረስሁ የተሰማኝ ልክ አንድ የመሬት መንቀጥቀጥ አካባቢውን አምሶ እንዳበቃ ያህል ነበር።"






ቤተ ሰቦቻቸው ቄስ ጉዲናን ለማግኘት በርካታ ጥረቶችን አደረጉ። ከወኅኒ ወኅኒ፣ ከፖሊስ ጣቢያ ፖሊስ ጣቢያ፣ ከከተማ ከተማ ተንከራተቱ ፍንጭ ግን አልነበረም። ጥረቱ በቀጠለበት ሰዓት ደርግ ባለቤታቸውን ወ/ሮ ፀሓይን አሰራቸው። የደርግ መንግሥት እንደ ወደቀ ፍለጋው እንደ ገና ቀጠለ። በርካታ ጥረቶች ተደረጉ፣ ሆኖም "አየሁ፣ሰማሁ" ባይ አልተገኘም። በመጨረሻም በወታደራዊው አገዛዝ ዘመን ከፍተኛ ባለ ሥልጣን የነበሩትና ሥልጣናቸው ከደኅንነት ጋር የተያያዘው ኮሎኔል ተስፋዬ ወ/ሥላሴ፣ ከጊዜው ርዝመት የተነሣ ትክክለኛ ቦታውን ለይተው ባያሳዩም ቄስ ጉዲና የተቀበሩበት ስፍራ ግን ልዑል አሥራተ ካሣ ግቢ እንደ ነበር ተናገሩ። በመጨረሻም፣ ቦታው 'እዚህ ነው' ባይ ስለ ጠፋ ተስፋ ተቈረጠ። ወታደር ከበደ አማረ፣ "የአፋልጉኝ" ጥያቄውን በሬድዮ እንደ ሰማ፣ የተቀበሩበትን ሥፍራ ለማመልከት ከደሴ ተነሥቶ መጣ። በመጀመሪያ ያመነው ሰው አልነበረም። የመንግሥት አካላት ካነጋገሩት በኋላ የሆነውን ሁኔታ ወ/ሮ ፀሓይ እንዲህ በማለት ይገልጹታል፤<<ከደኅንነት ቢሮ ስልክ ተደወለልኝና፣ 'ከበደ አማረ የተሰኘ ሰው ቄስ ጉዲና የተቀበሩበትን ቦታ፣ እንዴት እንደ ታሰሩና እንዴት እንደ ተገደሉ ለማሳየት ፈቃደኛ ሆኖ መጥቶአል' አሉኝ።" ማናችንም አላመንም። ሆኖም ዐብረን ተጓዝን፣ ተገድለው የተቀበሩበትን ቦታ አመልክቶን ቍፋሮው ተጀምሮ አንድ ሜትር ሳይርቅ ዐፅማቸው ተገኘ። በራስ ቅላቸውና በግዙፍ አቋማቸው እንዲሁም በደኅና ይዞታ በነበረው የእግር ሹራባቸው ለየናቸው።"

እንደ ከበደ አማረ አባባል፣ ቄስ ጉዲና ታፍነው በተወሰዱበት ምሽት የተገደሉት በገመድ ታንቀው ነበር። ሰኔ 21 ቀን 1984 ዓ.ም. የቄስ ጉዲና መገደል ይፋ ሆነ። ይህንን ተከትሎም ዐፅማቸው በክብር የሚያርፍበት ሁኔታ ይሰናዳ ጀመር። በቀብር ሥነ ሥርዐቱ ወቅት በርካታ ሰዎች የተገኙ ሲሆን፣ ታዋቂ ሰዎችም ስለ ሰብእናቸውና ስለ ተጋድሎአቸው የሚያውቁትን ተናግረዋል።

የሉተራን ጳጳስ ቄስ አርተር ዎልተር፣ በቀብሩ ሥርዐት ላይ ተገኝተው የቄስ ጉዲናን



የሕይወት ፈለግና የሰማዕትነት ተጋድሎ ባመላከተ ማስታወሻቸው እንዲህ ሲሉ አስፍረዋል፣ <<...አትርበድበድ፣ ወደ ማዕበሉ ግባና ርምጃ ውሰድ። በፍጹም ታማኝነት ትእዛዙን በምትጠብቅለት በእግዚአብሔር ታመን፤ በዚህ ጊዜ የነጻነትና የድል መንፈስ በልዩ ሐሤት ይቀበሉሃል።>>

ዲየትሪች ቦንሆፈር የተባሉ ጀርመናዊ የትምህርተ መለኮት ምሁር፣ እንደ ቄስ ጉዲና ቱምሣ ሁሉ በአሸባሪውና በአረመኔው የናዚ መንግሥት እጅ በወደቁ ጊዜ ከፍ ብለን የጠቀስናቸውን ቃላት ጽፈዋል። ሐሳቦቹ ነጻነትና እውነተኛውን ነገር ማክናወን መዛመዳቸውን ያስረዳሉ። <<...ሁከትና ስደት በበዛበት ጊዜ፣ ነጻነት የሚገኘው አንድ ግለሰብ ራሱን ለዐላማው ዋጋ አድርጎ ሲያቀርብ ብቻ ሲሆን ... ሰዎች ሲገፉ፣ የወንጌል አገልግሎትና የቤተ ክርስቲያንም ምስክርነት በዐመፅ ብዛት ሲገታ ጠንካራ ውሣኔና የማያወላውል አቋም መውሰድ ያስፈልጋል።>>

የአስተሳሰብ አቅጣጫዎችን ማብዛት የግድ አያስፈልግም። ነጻነት እውን የሚሆነው ርምጃ በመውሰድና ለእውነት በመቆም ብቻ ነው። ...የብዙዎችን ሕይወት ፍርሀት ስለ ገዛው ከኃላፊነታቸው ለመሰናበት ተገድደዋል። የሞት ብርታት የሚገለጠው እዚህ ላይ ነው። በ1966 ዓ.ም. የፈነዳው አብዮት ባመጣቸው ትርምሶች ውስጥ ቄስ ጉዲና ቱምሣ እውነተኛ የቤተ ክርስቲያን መሪ መሆናቸውን አረጋግጠዋል። በእግዚአብሔር ሐሳብ ላይ በመጽናት ያለ ፍርሀት የሆነ ርምጃ ለመውሰድ፣ ልባቸው የቈረጠ አቋም ሊወስዱ ተገደዱ። ለሰው ልጆች በነበራቸው ፍቅር በመመራት በተለይም ለተገፉት፣ በጣር ላይ ለወደቁትና ለቤተ ክርስቲያናቸው ሲሉ በተዋረዱት ፍቅር ተመርተው አቋም ለመውሰድ በቁ። ከካህናትና ከሥራ ባልደረቦቻቸው ጋር በመሆንም የሰውን ኀሊና በክሕደት መንፈስ ለማጥመቅ የቆመውን ማርክሳዊ ሥርዐት በቈራጥነት ተጋፍጠውታል። . . . በሕይወታቸው ላይ ከባድ የሥጋት ደመና ባንዣበበ ጊዜም እንኳ በኢትዮጵያ ውስጥ የቤተ ክርስቲያን እውነተኛ





እረኛ ሆነው መቈየትን መረጡ። ይህ ውሳኔ እርሳቸውንና ቤተ ሰባቸውን ውድ ዋጋ ጠይቋል።" የደቡብ አፍሪካው አቡን ዴዝሞን ቱቱ በበኩላቸው እንዲነበብ ያስተላለፉት መልእክት ፣ <<ስለ ጽድቅ የሚሰደዱ ብጹዓን ናቸው፤ መንግሥተ ሰማያት የእነርሱ ናትና>> የሚለው ነበር።

በርግጥ እነዚህ ሁሉ ሁኔታዎች ከመከሠታቸው ቀደም ብሎ በርካታ ወዳጆቻቸው ከኢትዮጵያ የሚወጡበትን መንገድ ያመቻቹላቸው ቢሆንም፣ በክህነት በሚያገለግሉት ሕዝብ ፊት ሰማዕትነትን መቀበል የመረጡ እኚህ ቄስ፣ ከየአቅጣጫው እየገደፈረ የመጣውን ሞት የተጋፈጡት፣ <<ከኢትዮጵያ እንድወጣ የሚያደርገኝን ኀጢአት አልሠራሁም>> በማለት ነበር። ሞተውም ያሸነፉት። ኢአማንያንን በማቀፍ የሚያምኑት ሥልጡን አማኝ በማያምኑ ሰዎች የመግደል እምነት እምነታቸው ሳይሞት መንገዳቸው ተደናቀፈ።

## <u>መወድስ</u>

**ፍትሕ ፈላጊ የእውነት ጠበቃ**
**ካህን ተጋዳይ የእግዚአብሔር ዕቃ**
**ጉዲና ቱምሳ ላመነው ኖረ**
**በነፍስ በሥጋ ተወዳደረ**

## <u>ትምህርተ ውልብታ</u>

**ለእውነት ለእኩልነትና ለፍትሕ ተሟጋች መሆን**

**አድልዎንና ዘረኝነትን ማስወገድ**



## <u>የውልብታ ምንጭ</u>

Aud sæveras, *In the Fiery Furnace*, Lunde publishers, (Trans lated by Harry T. Cleven,), Oslo, 1995

Eide, Øyvind M. *Revolution and Religion in Ethiopia*, Uppsala University,1996

Gudina Tumsa Foundation, *Witness and Discipleship, Leader ship of the Church in Multi-Ethnic Ethiopian in a time of Revolution*, The essential writings of Gudina Tumsa General Secretary of Ethiopia Evangelical Church Mekane Yesus (1929-1979) Addis Ababa.

________ *The life and ministry of Rev. Gudina Tumsa*, General Secretary of the Ethiopian Evangelical Church Mekane Yesus (EECMY), Addis Ababa, 2003.

Habtamu Bula, *"The Church should be a voice of the voice less"*, A short Biography of The Reverened Gudina Tumsa, Mekane Yesus Seminary, Addis Ababa, 1995

Dietrich Bonhoeffer, *Public opposition to the Nazi*, Online Exhibitions, *Ethiopian Pastor Speaks on Apartheid*, The Ethiopian Herald, Vol XXIX, No. 366, Tuesday, March 4, 1972.

ለሮን ቤኔት ጁኒየር፣ ማርቲን ሉተር ኪንግ ጁኒየር፣ የሕይወት ታሪክ፣ ታምሩ ፈይሣና ዶ/ር አያሌው ቀኖ እንደ ተረጐሙት፣ 1964 ዓ.ም.፣ አዲስ አበባ



ጌታቸው በለጠ፤ ኤሎሄ እና ሃሌሉያ፣ የኢትዮጵያ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ታሪክ (ቅጽ ሦስት1966 1992)፣ሚያዝያ 1992፣አዲስ አበባ



ቃለ ምልልስ ከዶክተር ተሰፋ ወርቅነህ ጋር ጳጉሜ 2 ቀን 1997 ዓ ም

ቃለ ምልልስ ከመምሬ ስለሺ ወልደ ሚካኤል ጋር መስከረም 27 ቀን 1998 ዓ ም

ቃለ ምልልስ ከአባ ጸጋዬ ቀንኒ ጋር የካቲት 30 ቀን 1999 ዓ ም

ቃለ ምልልስ ከዶክተር ደበላ ብሪ ጋር የካቲት 22 ቀን 1999 ዓ ም



## የአንባቢው የግል ማስታወሻ





# ፲፩



**ሰሎሞን ተሰማ**

**1926– 1972**

**ስለ ስፖርት ለፈፈ ሳይደክመው አረፈ**

*ማራቶን ማራቶን ማራቶን ልዕልቷ፣*
*አበበና ማሞ ሆኑ ባለቤቷ።*
*ማራቶን ደንግጠሽ አቤን ብትቈጪ*
*ዕድሏ የኛው ነች የትም አታመልጪ*

ከአዲስ አበባ አቧራማ ሜዳዎች ላይ የጨርቅ ኳስን ሲያንከባልሉና እንደ ልባቸው ሲጫወቱ ቈይተው የተዳከሙ ልጆች ሁሉ አደብ ገዝተውና ድካማቸውን ችለው በአንድ ትንሽ ልጅ ዙሪያ ይሰበሰቡ ነበር። ያ ትንሽ ልጅ ስለ እግር ኳስ ትንታኔ ይሰጣል። እንኳን እኩዮቹ ትልልቆችም አፋቸውን ከፍተው የሚሰሙትን የእግር ኳስ ዘገባ ያቀርባል። በትንሽ አድማጮች በአቧራማ ሜዳዎች የተጀመረው የጋዜጠኝነት ትእይንት ግን ውሎ አድሮ ለኢትዮጵያ የስፖርት ጋዜጠኝነትን ሙያ መሠረት ለመጣል በቅቷል።

ሰሎሞን ተሰማ የተወለደው አዲስ አበባ ውስጥ በ1926 ጥር ወር ላይ ነው። ከስፖርት ጋር ቁርኝቱን በሰፈር ውስጥ ጀመረ። ቀስ በቀስ የሰሎሞን የስፖርት ሙያ ሕልም ወደ ስኳውት አባልነት ሲተላለፍ የደበዘዘ መሰለ። በስካውት ውስጥ ሰሎሞን ተሰማ አዳፍኖት የነበረው ስፖርት እንደገና መቀስቀስ ሲጀምር በርካታ ትኩረትንና ብዙ ጆሮዎችን ይስብ ጀመር። በዚህ ሂደት መሃል ግን አባቱን በሞት ተነጠቀ። ወደ ታላቅ የስፖርት ዓለም ሰውነት የመንደርደር ሕልሙ ለጊዜውም ቢሆን የራሱንና የቤተ ሰቡን ኀላፊነት ለመሸከም በሚደረግ ትግል ውስጥ እንደገና የተዳፈነ መሰለ። የክብር ዘበኛን ሰራዊት ተቀላቀለ። ሰሎሞን ተሰማ ለአምስት ዓመታት ያህል በክብር ዘበኛ ሰራዊት ውስጥ በሬድዮ ኦፕሬተርነት ሠራ። በመቀጠል ደግሞ ወደ ቴሌኮሙኒኬሽን መሥሪያ ቤት በመዛወር 7 ዓመታትን በዚያ አሳለፈ ።

የሕይወት ውጣ ውረድ ጉዳይ ሆኖ ሰሎሞን ተሰማ በተጠቀሱት መሥሪያ ቤቶች በኩል ይለፍ እንጂ ነፍሱና እርሱ ዘላለም ከሚወሳባቸው ሕያው ሥራዎች ጋር ገና አልተገናኙም ነበር። በወቅቱ ወደ ማስታወቂያ ሚኒስቴር የፕሬስ ክፍል ሥራ ሲቀይር ግን ሰሎሞንና የሕይወት ጥሪው መቀራረብ ጀመሩ። ታታሪው ጋዜጠኛ፣ የጣጥምና የዜማ ደራሲ፣ ሕያው ያደረጉትን ሥራዎቹን ቀስ በቀስ ለማውጣት እንቅስቃሴውን ጀመረ። በተለይም ጋዜጦች የሰሎሞን ተሰማን





ጽሑፎች ይዘው መውጣት የተለመደ ተግባራቸው እየሆነ መጣ። በወቅቱ ብሥራተ ወንጌል የምሥራች ድምፅ ይባል የነበረው የሬድዮ ጣቢያም ለሰሎሞን ተሰማ በሳልና ማራኪ ስፖርታዊ ዘገባዎች የአየር ሰዓቱን ክፍት አደረገ።

የኢትዮጵያ የስፖርት ጋዜጠኝነት ሙያ መሠረት የሆነው ሰሎሞን ተሰማ በዚህ ሀይነት ወደ መገናኛ ብዙኃን መድረክ ገባ። በአንድ ወይም በሁለት ቦታዎች ሳይሆን በሁሉም የመገናኛ ብዙኃን ዓይነቶች ላይ በንቁ ተሣትፎና በማይዘነጋ ታታሪነት ስለ ስፖርታዊ ክሥተቶችና ትዕይንቶች በማራኪ ድምፅ መዘገቡን ቀጠለ ። ስለ ስፖርት ባይተዋር የነበሩ በርካታ ጆሮዎችና ሀይኖች ለሰሎሞን ተሰማ ዘገባዎች ትኩረት መስጠት ጀመሩ። በልጅነት እድሜው በሕፃናት ፊት ጣፋጭ የስፖርት ዘገባዎችን ያሰማ የነበረው ያ የመንደሩ ትንሽ ሕልመኛ ኢትዮጵያውያን ሁሉ ወደ ሚናፍቁት ትክክለኛ የሙያ ብቃት ተሸጋገረ።

ሰሎሞን ተሰማ በበርካታ የመገናኛ ብዙኃን የሚፈለግና ዘገባዎቹም ለጆሮ የማይጠገቡ፣ ለንባብ የማይሰለቹ ቊልፍ ሰው ሆነ። በወቅቱ በከፍተኛ ደረጃ በሚነበበው በአዲስ ዘመን ጋዜጣ የስፖርት ፋና ሀምዱ፣ በቴሌቪዥን የስፖርት ዘገባዎቹና በሬድዮን ዝግጅቱ ስፖርትንና ሰሎሞንን በጥምረት መመልከት ግድ እየሆነ መጣ። «የሰሎሞን ተሰማን የስፖርት ዓለም መሥዋዕትነት ለመግለጽ ቃላት ያጥረናል» በማለት በአንድ ወቅት ወንድሞቹ አቶ ተፈራ ተሰማ እና በቀለ ተሰማ ተናግረዋል። «ሰሎሞን ሌት ተቀን መሥራትን የማይሰለች እስትንፋሱን ከስፖርት ጋር ያስተሳሰረ ታማኝ ባለሙያ ነበር» በማለት ይገልጹታል።

በርካታ የመገናኛ ብዙኃን ባለ ሙያዎች በሚሠሩት የሚዲያ ሀይነት ጐልተው ሲወጡ ማየት የተለመደ ሊሆን ይችላል። የጋዜጠኛ ሰሎሞን ተሰማን ነገር ለየት የሚያደርገውና በርካታዎችን የሚያስገርመው ግን ልዩ ችሎታውና ታታሪነቱ ነበር። ሰሎሞን በቴሌቭዥንን፣ ሰሎሞን በሬድዮ፣



ሰሎሞን በጋዜጣ፣ በአጠቃላይ ሰውየው በሁሉም የመገናኛ ብዙኃን ላይ የተዋጣለት ድንቅ ባለሙያ ነበር። ሰሎሞን ተሰማ ፍጹም የተለያየ ባሕርይ ባላቸው ሦስት ሚዲያዎች ላይ በብቃትና በታታሪነት በሁለገብነት በመሥራት ይታወቃል። ይህንን ሁኔታ ከዛሬ ጋር ስናነጻጽረው የሰሎሞንን ግሩም ተሰጥዖ የሚያንጸባርቅ ይሆናል ምክንያቱም የተፈጥሮ ክህሎቱ ድጋፍ ሰጪ መሣሪያዎችና እውቀት በሌለበት ጊዜ እንኳ ዘመኑን የቀደመ ሥራ እንዲሰራ ጠቅሞታልና ነው። ሰሎሞን ተሰማ በኢትዮጵያ ጋዜጠኝነት ሙያ ላይ በአርአያነት የሚጠቀስ፣ ስለ ስፖርት ለበርካቶች ጆሮም፣ ዐይንም የሆነ ብቸኛ ሰው ነበር ለማለት ያስደፍራል።

በአገራችን በአሁኑ ሰዓት አንጋፋ የሚባሉ የስፖርት ጋዜጠኞች ሁሉ መሠረታቸውና መነሻቸው ሰሎሞን ተሰማ ነው ሊባል ይችላል። ለበርካታ ዓመታት ከሰሎሞን ዐደራውን ተረክቦ በተወዳጅና በማራኪ ድምፅ የኢትዮጵያን ስፖርት የሚዘግበው አንጋፋው ጋዜጠኛ ደምሴ ዳምጤ፣ "ጋሽ ሰሎሞን ድርጊቱ፣ ሁኔታው፣ እንቅስቃሴው ሁሉ ስፖርት ነበር። እሱ ለብዙዎች መነቃቃትን የመፍጠር ዐቅም የነበረው የማይዘነጋ፣ ከምንም ተነሥቶ ለዛ ያለውን ነገር ፈጥሮ የሚያሰማ ታላቅ ባለ ሙያና የሙያችን አባት ነው" ሲል ይገልጸዋል።

በቴሌቪዥን የስፖርት ፕሮግራም ሥርጭት የተጀመረው በጋዜጠኛ ሰሎሞን ተሰማ ነው። በወቅቱ በአፍሪካ አህጉር ከፍተኛ ተሰሚነትና ውጤት የነበራት አገራችን ኢትዮጵያ ለእግር ኳስ የነበራትን ንቁ ተሳትፎ በዋዐም ድምፁ የሚያዘክርና የሚያሰማ፣ አስደሳቹን ነገር የበለጠ የሚያስፈነድቅ አድርጎ የሚያቀርብ፣ አስደንጋጩን ክሥተት ደግሞ ልብን ከክሥተቱ ጋር እንዲከመሽሽ በሚያደርግ ሕያው ገለጻ ያደርስ የነበረው የሰሎሞን አንደበት ነበር። አገራችን በሦስተኛው የአፍሪካ ዋንጫ ላይ አስተናጋጅ በመሆን ብቸኛ የአፍሪካ ዋንጫ ድሏን አስመዝግባለች። ያንን ብቸኛ የአፍሪካ ዋንጫ ድል የማይዘነጋ ኀሊና ባለቤት





የሆነ ስፖርት አፍቃሪ ሁሉ የድሉን ዜና በማራኪና ቁጭ ብድግ በሚያሰኝ ገለጻ አሳምሮ ያቀረበውን ኢትዮጵያዊ የስፖርት ዓለም ሰው ምንጊዜም አይዘነጋውም። ዛሬም ድረስ ከሦስተኛው የአፍሪካ ዋንጫ ድል ጋር የሰሎሞን ተሰማ ሕያው ድምፅ አብሮ ይሰማል።

በቅርቡ ከዚህ ዓለም በሞት የተለየን ሌላው አንጋፋ የስፖርት ጋዜጠኛ ጕርፍነህ ይመር ከረፍቱ በፊት ስለ ሰሎሞን ተሰማ ባለ ውለታነትና ታታሪነት ምስክርነቱን ሰጥቶን ዐልፏል፤ «አስቸጋሪ በሆነው የሬድዮ ተንታኝነት ሳይቀየር በዘመኑ በብቃት የሠራ ለአገሪቱ የስፖርት ጋዜጠኞችና ለዘመኑ ስፖርተኞች የማይዘነጋ መሥዋዕትነትን የከፈለ» በማለት ሰሎሞን ተሰማን ገልጾታል።

ታላቁ የስፖርት ጋዜጠኛ የዜማና ግጥም ደራሲ ሰሎሞን ተሰማ ስለ ስፖርተኞችና ስለ ስፖርት የሚያየውን ብቻ መዘገቡንና ማስተላለፍን የሚመርጥ ጋዜጠኛ አልነበረም። ስፖርተኞች ከስፖርት ውጪ ያለ ሕይወታቸው ምን ይመስላል? እንዴት ይኖራሉ? ምን ይበላሉ? ምንስ ይጠጣሉ? የሚለውን ለማወቅ የሚተጋም «ውስጥ አዋቂ» ጋዜጠኛ ነበር።

እንደ አሁኑ ስፖርተኞች በአንጻራዊ የተሻለ ክፍያ በማያገኙበት ወቅት ለሰሎሞን የሕዝብ ዕውቅናና የሙያ ስኬት ትልቅ ክፍያ እንደ ሆነ ለሚወደው ሕዝብ ማስረዳት ሥራው ነበር። በዚያን ወቅት አንድ ሆኖ ሳለ እንደ ብዙ ኢትዮጵያውያን ፊር ቀዳጅ ባለ ድሎች የብዙዎችን ገድል ለመተረክ ሰሎሞን ተሰማ ሰንፎ አያውቅም። የማይረሱ ድሎች በማይረሱ ዘገባዎች፣ የማይዘነጋው የአትሌቶች ዓለም ክሥተት በማይሰለቸው የሰሎሞን ተሰማ ድምፅ ለዓመታት ተነግሯል። ለዚህ ድካምም ሆነ መስልቸት ላልታየበት አስደናቂ ተግባሩ ደግሞ ኢትዮጵያውያን አትሌቶች፣ የስፖርት መሪዎችና ታዋቂ ግለሰቦች ሕያው ምስክርነት የሰጡበት ተደጋጋሚ አጋጣሚ አለ።



ለምሳሌ፦ ወደ ሜክሲኮ ሲቲ ኦሎምፒክ በትዝታ እንመለስ። በሮምና በቶኪዮ አበበ ቢቂላ ማራቶንንና ኢትዮጵያን፣ ማራቶንንና አፍሪካን በወርቅ ካስተሳሰረ በኋላ ሜክሲኮ ሲቲ ላይ ሀደራውን ለማሞ ወልዴ በመስጠት አቋርጦ ወጣ። ማሞ ወልዴ በሜክሲኮ ሲቲ አደባባይ የኢትዮጵያንና የአበበን ሀደራ ተቀብሎ ሲሮጥ ግን ብቻውን አልነበረም። የድምፅ ማጉያ በመያዝ ማሞን የሚያበረታታ፣ ምን ያህል ኪሎ ሜትር እንደ ሮጠና ምን ያህል ኪሎ ሜትር እንደ ቀረው ለማሞ የሚናገር አንድ ሰው ነበር። ያ ሰው ጋዜጠኛ ሰሎሞን ተሰማ ነበር። ማሞ ወልዴ ሜክሲኮ ሲቲ ላይ የኢትዮጵያን ሰንደቅ ዓላማ በማራቶን ድል እንዲውለበለብ ካደረገ በኋላ ለተገኘው አንጸባራቂ ድል የሰሎሞን ተሰማ ዕገዛ ከፍተኛ መሆኑንም፣ «ከጀርባዬ በመሆን እየተከተለ ያበረታታኝ ነበር። ሰሎሞን ተሰማ ምን ያህል ኪሎ ሜትር እንደሚቀረኝና እንዴት መጨረስ እንዳለብኝ በመምከር ለድሉ ወሳኙን ድርሻ ተወጥቷል።» በማለት መስክሯል።

የኢትዮጵያ የኦሎምፒክ ዓለም ተሳትፎ በ 1956 ዓ.ም ሜልቦርን ላይ ይጀመር እንጂ አገራችንን ለመጀመሪያ የወርቅ ሜዳልያዎች ያበቋት የአበበ ቢቂላ የሮም እና የቶኪዮ የማራቶን ድሎች ናቸው። አበበ ከማራቶን ድሉ በኋላ አዲስ አበባ ሲገባ ልክ በቅርቡ የኦሎምፒክ ውድድሮች ላይ እንደሚታየው ሕዝቡ በነቂስ በመውጣት አቀባበል አድርጎለት ነበር። ያንን የአቀባበል ትዕይንት ሲያስተላልፍ የነበረው ጋዜጠኛ ሰሎሞን ተሰማ እንደ አበበ የባዶ እግር ሩጫ ድል ሁሉ የማይረሳ አሻራን በሙቀው ዐልፏል። አበበ ቢቂላ ይጓዝበት የነበረውን መኪና፣ ሕዝቡ ስለ አበበ ያሳየውን የሞቀ አቀባበልና የአበበ ቢቂላን ስሜት ጋዜጠኛ ሰሎሞን የገለጸው ደግሞ ደጋግሞ ቢታይ እንዳይሰለች አድርጎ ነበር ። ከዚህ የተነሣ፣ በርካቶችም «የመረጃ ፍሰት ባልነበረበት ሰዓት የስፖርት ጋዜጠኝነትን ጠንቅቆ በመረዳት ቀድሞ የተፈጠረ ሰው» ሲሉ ጋዜጠኛ ሰሎሞንን ያወድሱታል።



ለኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን ለአፍሪካ



ስፖርት አባት ተብለው የሚወደሱት አቶ ይድነቃቸው ተሰማም የጋዜጠኛ ሰሎሞን ተሰማን ከፍተኛ ችሎታና ብቃት በየጊዜው የሚያደንቁ ሰው ነበሩ። «አትሌቶች ራሳቸው ሮጠው ያሸንፉ እንጂ ሁሉም ከእነርሱ ጋር የሚሮጥ እነሱን የሚያነቃቃና የሚያበረታታ ሰው አለ። ሰሎሞን ተሰማ በእነ አበበ በእነ ማሞና በእነ ምሩጽ ይፍጠር ድል ውስጥ ጉልሕ ድርሻ አለው» ። ብለዋል።

ጋዜጠኛ ሰሎሞን ተሰማ በወቅቱ ለዘገባ ከአገር በሚወጣበት ወቅት በሌሎች አገሮች ስፖርትና ስፖርተኞች ላይ የሚታዩ ጠንካራ ነገሮችን ወደ አገር ውስጥ ለማምጣት የሚሞክር ፍጽሞ የማይሰለች ጋዜጠኛም ነበር። አንጋፋው የቀድሞው የኢትዮጵያ ሬድዮ የስፖርት ጋዜጠኛ ይምበርበሩ ምትኬም በአንድ ወቅት፣ «ሰሎሞን የማይሰለች ተአምረኛ ሰው ነው፤ ለአዲስ ነገር አይሰንፍም ልዩ ተሰጥዎና ታታሪነት ተችሮት የተወለደም ይመስለኛል። በአጠቃላይ ለኢትዮጵያ ስፖርት በቀላሉ የማይታይ ውለታን ሠርቶ ያለፈ ባለ ሙያ ነው።» ሲል ገልጾታል።

የተለያዩ ሰዎች ምስክርነት እንደሚያስረዳው፣ የጋዜጠኛ ሰሎሞን ተሰማና የስፖርት ዓለም የጠበቀ ትስስር በሰርጉ እለት እንኳ ስታዲየም አስገብቶታል። ሰሎሞን ተሰማ ጋብቻውን በፈጸመበት ዕለት በአዲስ አበባ ስታዲየም የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድን የናይጄሪያ አቻውን ለአፍሪካ ዋንጫ ማጣሪያ ያስተናግድ ነበር። ሁለንተናውን ለኢትዮጵያ ስፖርት የሰጠው ጋዜጠኛ ሰሎሞን ተሰማ አጃቢዎቹን አስከትሎ በመንሽራሸር ፊንታ ከበርካታ ጓደኞቹና ከባለቤቱ ጋር አዲስ አበባ እስታዲየም ነፍሱ ለዓመታት የታመነችለትን ስፖርት ለመመልከት ተገኝቷል። ሰሎሞን ልቡንና ጊዜውን በሙሉ ለስፖርት ዘገባዎች በመስጠት ያለፈ ሰው ነው። አረንጓዴው ጉርፍ በውጪ ውድድሮች ላይ የማይደበዝዝ ደስታ ሲፈጥር ሰሎሞን በበኩሉ የማይዘነጋ ሙያዊ ዘገባ ሠርቷል። የወቅቱ የኢትዮጵያ ኀያል የእግር ኳስ ቡድን ባሸነፈ ቍጥር፣ የሰሎሞን ተሰማ ብርዕና እንደበት የስፖርቱን ሕያው ጀግኖች



ውለታ በመዘከር ለሕዝብ በማስተዋወቅ ተግተዋል።

ሰሎሞን ውስጠ ትኩስ የጋዜጠኛነት ተሰጥዎ ያለው ሰው ብቻ ሳይሆን የላቀ የምግባር ዕሴት የሚታይባቸውን የዘፈን ግጥሞች ለዘመኑ ምርጥ ድምፃውያን ያቀበለ ሰውም ነበር። ለምሳሌም፦ እንደ ተወደደች ሳለፈችው ለብዙነሽ በቀለ «የእናት ውለታዋ»፣ «የሚያስለቅስ ፍቅር»፣ «የሰው ነገር በቃኝ» ፣ ለታዋቂው ድምፃዊ ለጥላሁን ገሠሠ ደግሞ «ሞናሊዛዬ ነሽ»፣ «ለእውነት እሞታለሁ» እንዲሁም ለድምፃዊት ኂሩት በቀለ «ባህል እንዳትጠፋ» ፣ «እሎሚዬ» የተሰኙት የዘፈን ግጥሞች የዚሁ ተወዳጅ የስፖርት ጋዜጠኛ የብርዕ ጠብታዎች ናቸው። ይሁን እንጂ ከሁሉ መረሳት የሌለበትና ከእርሱ ቀጥተኛ ሙያ ጋር በጽኑ የሚቈራኘው የሚከሰኮ ኦሎምፒክ የወለደውና የወትቱ የስፖርት ማኅበረ ሰብ የማይዘነጋው «ማራቶን ልዕልቷ» የተሰኘው የስፖርት ዜማው ነው። ከዜማው ግጥም አራቱ ስንኞ የሚከተሉት ናቸው፦

ማራቶን ማራቶን ማራቶን ልዕልቷ፣
አበበና ማሞ ሆኑ ባለቤቷ።
ማራቶን ደንግጠሽ አቤን ብትቈጪ.
ዕድሏ የኛው ነች የትም አታመልጪ.

እንደ በሳል የስፖርት ዘገባዎቹ ሁሉ የሰሎሞን ዜማና ግጥሞችም ዘመን አይሽሬ ናቸው። ጊዜያትን ዘለዋል። ዛሬም ለአዲሱ ትውልድ አዲስ ትርጉም ይሰጣሉ። ቢደመጡ አይሰለቹም። የሙዚቃ ግጥምና የዜማ ደራሲነቱን የሚያደንቀው እንጋፋው አቀንቃኝ ጥላሁን ገሠሠ በአንድ ወቅት የሰሎሞን ተሰማን ሕይወት አስመልክቶ በተሠራ የቴሌቬዥን ፕሮግራም ላይ «ሰሎሞን እንደ ስፖርት ጋዜጠኛ የማይረሳ፣ የሰው ልብ እንደ ፈለገ በቃላት የሚሰቅልና የሚያወርድ ሰው ነበር» በማለት ገልጾታል። ከበርካታ የአገራችን የሙዚቃ አፍቃሪዎች ኅሊና የማይጠፉት እነዚህ መልእክት ዐዘል ዜማዎች የሰሎሞን ተሰማን ሌላ የጥበብ ሥጦታ የሚመሰክሩ ሕያው ሥራዎች ናቸው።





ሰሎሞን ተሰማ ከዚህ ዓለም በሞት የተለየው ገና ብዙ መሥራት በሚችልበት ዕድሜው ነው። በቈየባቸው 46 ዓመታት መሠረት ጣይ ሥራዎችን ሠርቶ ቀሪ ቅርስ ትቶ አልፏል። ከምንም ነገር ላይ በመነሣት ለዘመናት የስፖርት ዓለም ጋዜጠኞች የሚሄዱበትን መንገድ ነድፏል። በማይዘነጋ ታታሪነትና መሥዋዕትነት በሦስት ዓይነት የመገናኛ ብዙኃን ላይ ብዙ ሰው የሚሠራውን ሥራ ለብቻው ሠርቷል። ለኅሊናችን ጓደኛ፣ ለጆሮአችንም ጣፋጭ የሆኑ የኪነ ጥበብ ሥራዎችን ከትቦም አልፏል። ራሱን በአንድ ዓይነት ሥራ ብቻ ሳይገድብ በየሙያ መስኩ በትጋት ባከናወነው አኩሪ ተግባር ምሳሌነቱን አስመዝግቧል።

ሰሎሞን ተሰማ ሕይወቱ ካለፈ ከበርካታ ዓመታት በኋላም በብዙ ሰው ልብ ውስጥ አለ። ትውልድ በትውልድ ቢተካም የዚህን ታላቅ ባለሙያ አሻራ ከመደምሰቅ ያስቀረው አንዳች ነገር የለም። በኢትዮጵያ የኦሎምፒክ ታሪክ የመጀመሪያውን የድል ምዕራፍ ከከፈተው ከአበበ ቢቂላ መቃብር ፊት ለፊት ሐውልት ቆሞለታል። ይህ ውሳኔ ሁልጊዜ ትክክል ውሳኔ ነው። ምክንያቱም ቦታው የሁለት ሕያውና ፋና ወጊ የሆኑ ደማቅ የሙያ ጀግኖችን ትስስር ይመሰክራልና።

ገና ከልጅነት እድሜው የጀመረውን የሙያ ፍቅር አሳድጎ ወደ ታላቅ ስኬት የቀየረው ጋዜጠኛ፣ የዜማና የግጥም ደራሲ ሰሎሞን ተሰማ ለሚወዳቸውና ሕያው ስም እንዲኖረው ላደረጉት ሥራዎቹ እንደ ሮጠ፣ መሥዋዕትነትን እንደከፈለ አልፏል። ለኢትዮጵያ ስፖርት ዘመን ተሻጋሪ ሥራ ለሠሩ ኢትዮጵውያን የስፖርት ዓለም ሰዎች ራሱን አሳልፎ ሰጥቷል። በመጪው ጊዜም ሳይታክት እንደ ሮጠ ያለፈውን ሕያው ሰው ውለታ ማስታወስ ይቀጥላል። ሰሎሞን ተሰማን!



## መወድስ

ስፖርት በኢትዮጵያ ነቅቶ እንዲንሰራፋ
በወጣትነቱ ብዙ ጣረ ለፋ

ሰሎሞን ጠቢቡ ባለ ብዙ እውቀት
ምነው ትንሽ ቢኖር ላገራችን ስፖርት

ሲሮጡ አብሮ ሮጦ ሳይሸለም በሩጫ
በርቺ በርታ አለ ሌላ እንዲያገኝ ዋንጫ

ደማቁ ሰሎሞን ስለ ስፖርት ለፈፈ
ብዙ ሮጦ ሮጦ ሳይደክመው አረፈ

## ትምህርተ ውልብታ

ትጋትና ታታሪነት

አንድን ሙያ በተለያየ አቅጣጫ መተግበር መቻል

የሙያ ፍቅር ብቃትንና ስኬትን ለማምጣት ያስችላል



ያለንን ተሰጥኦ ማዳበርና ለሌሎች በሚተርፍና ለውጥ በሚያመጣ መልክ ተስፋ ሳይቆርጡ መተግበር



## የውልብታ ምንጭ

«ሰሎሞን ተሰማ»፣ በጋዜጠኛው የሕይወት ታሪክ ዙሪያ የተሰናዳ ያልታተመ ጽሑፍ፣ 1994

ከጋዜጠኛ ጕርፍነህ ይመር ጋር የተደረገ ቃለ ምልልስ ፣ አዲስ አበባ ስታዲየም የካቲት 15 ቀን 1999

የአንጋፋ ጋዜጠኞች ስለ ጋዜጠኛ ሰሎሞን ተሰማ የሰጡት አስተያየትና ቃለ ምልልስ (1993-1994)

ዐውደ ሰብ የቴሌቪዥን ፕሮግራም አስፋው ፈቃደ፣ «ያልተሸለመው ሯጭ» ጋዜጠኛውን አስመልክቶ የተሰራ ፕሮግራም፣ 1994

Wikepedia the Free Encyclopedia. Profile of Solomon Tessema





## የአንባቢው የግል ማስታወሻ





# ፲፰



**ጸጋዬ ገብረ መድኅን**
**1929–1998**
**ማኅደረ ሺክስፔር ትምክሕተ አፍሪካ**

*የማይነጋ ህልም ሳልም*
*የማይድን በሽታ ሳክም*
*የማያድግ ችግኝ ሳርም*
*የሰው ሕይወት ስከረክም*
*እኔ ለኔ ኖሬ አላውቅም*

*ጸጋዬ ገብረ መድኅን*

አቶ ገብረ መድኅን ሮባ ቀዌሳ ነፍስ ጡር ባለቤታቸውን ወይዘሮ ፈለቀች ዳኜ ኀይሉንና ቀዬአቸውን ጥለው በፋሽስት ኢጣሊያ ወረራ ከተቈጣው የኢትዮጵያ ሰራዊት ጋር አፄ ኃይለ ሥላሴን ተከትለው ተመሙ። በወርኀ መስከረም 1929 ዓ. ም. ከአምቦ 30 ኪሎ ሜትር ርቃ በምትገኘውና ቦዳ በተሰኘችው የገጠር መንደር አባ ወራው በሌሉበት ወይዘሮ ፈለቀች ዳኜ የጥበብ ጸጋ የሆነውን፣ ጸጋዬ ገብረ መድኅንን ለኢትዮጵያ፣ ለአፍሪካና ለዓለም ሰጡ። ይህ ሕፃን በኢትዮጵያ የትያትር ታሪክ አንዳች አሻራ ይተዋል፤ ሼክስፔራዊ የግጥም ስልትና አፍሪካዊ የኀሊና ስሌት ፈለግ ያኖራል፤ በኪነ ጥበብ ዓለምም የማይጠፋ ቅርስ ይተክላል ብሎ ያኔ ማን አሰቦ! እንዲያው ብቻ በአምላክ ጸጋ ይደግ ተባለ እንጂ። ዳሩ «ስምን መልአክ ያወጣዋል» ይባል የለምን?

ለፋሽስት ያደሩ ባንዶች የገብረ መድኅንን ጎጆ እሳት ቢጭሩበት፣ የሕፃኑ ዕጣ ፈንታ ከቤተ ሰቡ ጋር ዘመድ ቤት መጠጋት ሆነ። በፋሽስት ወረራ የጦር ድባብ ተወልዶ የአገሩን ምጥ ጣር ትንፋሽ ምጎ አደገ፤ ከአማራም ከኦሮሞም ደሙን ቀዳና የዘር የጎሣ መስተጋብሪያ ድልድይ ሆነ።[1] ኦሮምኛን ከተወለደበት ቀዬ፣ ዜማንና ቅኔን ከቤተ ክህነት[2] ቀሰሚል። «ከዚህም በመውጣቴ የተሟላሁ ኢትዮጵያዊ ነኝ ... የተለያዩ ባህሎችን ለማጥናት የገፋፋኝም ይኸው ነው። በቅኔዎቹም ይህንን ሁሉ እንጸባርቃለሁ» ያለን ለዚህ ነው ። ፈጥኖ ያንቈረቈረውን የእንግሊዝኛ ቋንቋም ከጊዜው አስኳላ ለቀመው። ውሎ አድሮም ፈረንሳይኛ ተናጋሪ ሆነ።

[1] አባቱ የሚጫ ሰው እናቱ ደግሞ እንከበሬ ናቸው
[2] ዳዊት የደገመው ከአለቃ ብሥራትና ከአባ ወልደ ማሪያም እግር ሥር ቁጭ ብሎ ነው






ጸጋዬ ከዘመን ምዕራፎች በኋላ የልጅነት እስተውሎቱን እንዲህ ብሎ ያስታውሳል፦ «በልጅነቴ ከእናቴ ጋር ብርሌ ይገፔ ማሪያም ማኅበር ስሔድ እዚያ ያሉ እናቶች ከጠላ ጋር ባሕርያቸው ሲለወጥ የሙሴውና የካህኑም ባሕርይ ሲለወጥ ይኼ በውስጤ እድሮ ሥዕል ስለሚፈጥርብኝ እሰላስዬው ወይም አመንዥኬው እድሬ ጠዋት በግድ በብርዕ አወጣዋለሁ... »። ስለ ልጅነት ዘመን የትምህርት ቤት ትውስታውም ሲናገር «በሰባትና በስምንት ዓመቴ የጻፍኳቸውን ግጥሞች በክፍል ውስጥ ለአስተማሪዎቼ ሳነብ፣ 'እንዲህ ነው አጻጻፍ' ብለው ራሳቸው በንባብ ያበረታቱኝ ነበር። በተለይ የቅኔ ሊቅ የነበሩት የዲማው አለቃ መምህር ዮሐንስ ፣ አምቦ በመንግሥት ትምህርት ቤት ውስጥ እሳቸው ወንበር ላይ፣ እኔ ደግሞ መደብ ላይ ቁጭ ብዬ ሲያስተምሩኝና ግጥሞቼን ሲያቃኑልኝ 'ይህች ስስ ናት፣ ይህ ደግሞ ያጣላሃል፥ ይህ ግን ውብ ነው'ይሉኝ ነበር። »

እዳጊው ወጣት ጸጋዬ የኪነ ጥበብን ዕልፍኝ ሊጓደድባት ገና ከጠዋቱ በሯን የከፈተው በ1942 በአምቦ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ንጉሥ ኃይለ ሥላሴ በታደሙበት መድረክ «የዳዩናሲስ ዳኝነት» በተሰኘው ድራማው ነበር።[3] ይሁን እንጂ የዚህኛው ታሪክ መክፈቻ ለመጪው የጸጋዬ ሙያ ራሱን የቻለ ዋዜማና የመዘጋጃ ዓመታት ነበሩ። ጸጋዬ እነዚያን ዓመታት እንዲህ አልፎባቸዋል፦

[3] ለዚህ የመጀመሪያ ድራማው ቆስቋሽ ምክንያቱ በጊዜው ወላጆቹ ገጥሟቸው በነበረ የፍርድ ቤት ክርክር ጉቦ ባለ መስጠታቸው ደርሶባቸው የነበረው የፍትህ መጓደል እንደ ነበረ ሞልቬር ይጠቅሳል
Molvaer, Reidulf K., *Black Lions: The Creative Lives of Modern Ethiopia's Literary Giants and Pioneers*, Lawrenceville: The Red Sea Press, Inc., 1997 271.



...የስምንት ዓመት ጋሜ ልጅ ሆኜ አባቴ በማለዳ ተነሥተው በአንድ እግራቸው ቆመው ከጸለዩ በኋላ ከብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደ ሥላሴ መጽሐፍ ውስጥ ድምፃቸውን ከፍ አድርገው 'ወዳጄ ልቤ ሆይ የአንተ መከራ የእኔ መከራ አይደለምን?' የምትለዋን ብዙ ጊዜ ይደጋግሟታል። ወዲያው የትምህርት ቤት ደወል ሰምቼ የሁሉቃን ወንዝ በሩጫ አቋርጬ ትምህርት ቤት እደርሳለሁ። የአማርኛና የሥነ ጽሑፍ አስተማሪዬ የዲማው አለቃ ማእምር ዮሐንስ ለሐምሌ 16 የጃንሆይ የልደት በዓል ዋዜማ ወይም ለሚያዝያ 27 የነጻነት በዓል ዋዜማ ወይም ለየካቲት 23 የዓድዋ ድል በዓል ዋዜማ የክቡር ባለ ቅኔ ከበደ ሚካኤልን «እሮሮ እና ነጻነት» የተባሉ ሁለት ሥነ ግጥሞች ለተማሪ ካህሁን ማህሌና ለተማሪ ጌታቸው ተክለ ሃይማኖት በጎላ ድምጽ ሲያስጠኗቸው እደርሳለሁ። እዚያው እንደቆምኩ እኔም ግጥሞቹን በቃል አጠናቸዋለሁ። በማግሥቱም በበዓሉ ላይ ሕዝብ በተሰበሰበበት አገር ገገርውና የከተማው አንጋፋ ሰዎች በተገኙበት ግጥሙን ያጠኑት ድምፃቸውን አጉልተው ሲያነበንቡት እኔም ከተማሪዎች ጓደኞቼ ጋር በሰልፍ መካከል ቆሜ በጸጥታ ድምፅ ከእነርሱ ጋራ አነበንበዋለሁ። እቤት ስገባም አባቴ ፊት ቆሜ «እስቲ ጸጌ ያን በአደባባይ የሰማነውን ግጥም አንብብልኝ» ሲሉኝ በጐላ ድምፅ በቃሌ እወጣላቸዋለሁ። ማናቸውንም ጽሑፎችና የወደቁ ወረቀቶች የአባቴን መልክአ ማርያምና ሌሎች ሰነዶች ማጥናት ማንብነብ፣ መጣጥፍ ብጤ በግጥም መጫርና መሠረዝ የጀመርሁት በዘጠኝ ዓመቴ ነበረ።

እምቦ ላይ የነበረውን ጸጋዬን አዲስ አበባ ጠሩትው፤ ሊላ ቢሆንልኝ ብላ፣ በጀኔራል ዊንጌት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤትና በንግድ ሥራ ትምህርት ቤት አሳልፋ ሞከረችው። ጸጋዬ የአገር ውስጥ ትምህርቱን በኪነ ጥበብ ነፍሱ አስተናግዶ ከቺካጎ ብላክ እስቶን ስኩል ኦቭ ሎው የሕግ ዲግሪ አግኝቷል። ከዚያም ኪነ ጥበብ የነፍስ የሥጋው ረኃብ (ጥማት) ሆና ሳበችውና የለንደን ሮያል ኮርት ትያትርን ፣ የፓሪሱን ኮሜዲ ፍራንሲየስ፣ ከዚያም ወደ ሮም በመሄድ የኪነ ጥበብ ጣዝማውን ሲቀምም ቈይቷል።





በተማሪነት ዘመኑ የለንደን ሮያል ኮርት ትያትር ባደረገለት ግብዣ መሠረት 'የአዳም ምርኩዝ' እና 'የእንጨቱ ሱቅ' የተሰኙ የአፍሪካን ሁኔታ የሚያሳዩ ተውኔቶችን በማቅረብ ችሎታውን አስመሰከረ።

ከለንደን ትምህርቱን አጠናቆ የመጣው ጸጋዬ በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ቴአትር ቤት የኪነ ጥበብ ዴሬክተር ሆኖ እንዲያገለግል በ1954 ተመረጠ። በዚህ ጊዜ ነበር ጸጋዬ ብዙ የጽሑፍ ሥራዎች የሚያመርት ጸሓፊ ወደ መሆን የመጣው። ከ1953 እስከ 1962 ባሉት ዘጠኝ ዓመታት ብቻ 12 ተውኔቶችን ጻፈ፤ ተረጐመ። ከእነዚህም መካከል «ጆሮ ደግፍ፣ በልግ፣ ሐሙሌት፣ ማክቤዝ፣ እኝ ብዬ መጣሁ፣ የከርሞ ሰው፣ ጴጥሮስ ያቺን ሰዓት፣ ክራር ሲከር፣ የፌዝ ዶክተርና አወናባጅ ደብተራ»ን ለሕዝብ እይታ አበቃ። ከዚያም በኋላ በተፈጠሩ አንዳንድ ችግሮች የተነሳ ከታኅሣሥ 1962 እስከ የካቲት 1966 ዓ.ም. ድረስ እሱም ሆነ ሥራዎቹ ከትያትር መድረክ ፊታቸውን አዞሩ።

አቶ አስፋው ዳምጤ (ሓያሲና ደራሲ) ከጸጋዬ ጋር የተዋወቁት እንዲህ ነበር፤ ናቸው።

በ1951 ዓ.ም. የዩኒቨርስቲ ኮሌጅ ተማሪ በነበርኩበት ጊዜ ከፕሮፌሰር ዩናስኪ ጋር በዩኒቨርስቲው ቤተ መጻሕፍት ውስጥ ይሠራ ነበርና እኔ ስመላለስ አየው ነበር። በቤተ መጻሕፍቱ ውስጥ የነበሩ ተጠቃሚዎችና መሪዎች በአብዛኛው ፈረንጆች ሲሆኑ ጥቁር ሠራተኛ እርሱ ብቻ ነበር። ያኔ ምንም ትውውቅ አልነበረንም። ኋላ በትምህርት ሚኒስቴር በሥርዓተ ትምህርት ክፍል ሦስት ተውኔቶቹን ልኮ ኖሮ እኔ እንድገመግመው ደረሰኝ። አንብቤ በጣሙ ወደድኳቸው። መጀመሪያ የደራሲውን ማንነት አላወቅሁም። ከድርሰቶቹ አንዱ «ሊላው አዳም» ነበር። ሌሎቹ ምን እንደ ነበሩ ረስቻቸዋለሁ። ተውኔቶቹን ሳነብ እሱ የጻፋቸው ተውኔቶች ለትምህርት ገበታ መጻሕፍትነት የማይሆኑ መሆኑን አስታውሳለሁ። ከሁለት ዓመት በኋላ በ1953 ዓ.ም. እንግሊዝ አገር በተማሪነት ተገናኝተን ስንጫወት እንዴት እንዳነሣነው ሳላውቅ ስለ ገመገምኳቸው ሦስት



ተውኔቶች ነገርሁት። ይሄኔ «አንተ ነበርካ ሳንሱሬ» አለኝ። «ያንተ ኖሯል እንዴ» ስለው፣ «አዎ» አለኝ፤ ተግሥቀን ተለያየን።

አቶ አስፋው ዳምጤ የጋብቻ ሥርዓት በሚፈጽሙበት ጊዜ የመጀመሪያ ሚዜ ካደረጉት ከጸጋዬ ገብረ መድኅን ጋር በ1951 ዓ.ም. የዩኒቨርስቲ ኮሌጅ የሦስተኛ ዓመት ተማሪ በነበሩበት ጊዜ በእንዲህ ዓይነት መልኩ በዐይን እንደሚተዋወቁና፣ 1953 ዓ.ም. በእንግሊዝ ከተገናኙ በኋላ ጓደኛ እንደነበሩ በመግለጽ ስለ ጸጋዬ በተጨማሪ ሲናገሩ፡-

> ጸጋዬ የተጐዳ፣ በሕይወትም በሰዎችም የተደቈሰ ሰው ካገኘ የመደገፍ ስሜት አለው። የሕዝብ ወገን ነው ማለት ይቻላል። የደረሰበትን ዕውቅና ያገኘውና እያንዳንዷን እርከን ያለፈው እያስመሰከረ ነው። እሱን ለማደናቀፍና ጠልፎ ለመጣል በአስተዳደራዊ ዘርፍና በሙያ ተቀናቃኞች ብዙ ተደርጐበታል። አንድ ነገር ሲፈጸምበት 'ለምንድን ነው የማይተወኝ' እያለ እሪ ይል ነበር። 'የአደባባይ ሰው ስለ ሆንህ የማንም ሰው ጥሬ ዕቃ ነህ፤ እንደፈለጉት አበጃጅተው ጥሩ ሥዕል ሊያወጡብህ እንደሚችሉ ማወቅ አለብህ፤ ይተውኝ ካልክ መድረክ ላይ አለመውጣት ነው' እለው ነበር። አንድ ጊዜ ጃንሆይ ጠርተውት፣ 'ስለ ትያትር በኢትዮጵያ ምን መደረግ አለበት? ጽፈህ አምጣ' ብለውት ጽፎ አቅርቧል። ይሄን የሚሰሙ አለቆቹና የአለቆቹ አለቆች እንዴት እንደሚሰማቸው መገመት ይቻላል። ... ጸጋዬ መሽቀርቀር አይወድም። ግን ጥራት ያለውን ልብስ ነው የሚለብሰው፡፡ ብርድ ስለማይችል ነው ካፖርት፣ ወፈር ያለ ልብሶችን የሚወደው። በምግብ ምርጫም ጉበዝ ነበር። ከተማ ምግብ ለመብላት ስንፈልግ የእርሱ ምርጫ የተሻለና የምንወደው ዓይነት ነው ...



አንዴ የፈጣሪ ትሩፋት የሆነችውን ኪነ ጥበብ ከእርሱ ከፈጣሪ ከተሸለመ በኋላ ለካስ እሷው ራሷ ማኅደረ ሽልማት ሆና ኖሮ ዘመኑን ለሽልማት እንዲኖር አድርጋዋለች። ደስ የሚሉም የሚያሡቅዩም ሽልማቶች ለሷው ከሷው



በሷው የተነካ ተሸለመላት፣ ተሸለመባት። የ13 ዓመቱ አዳጊ ወጣት ለንጉሥ እይታ ያበቃው «የዳዩናሲስ ዳኝነት» የተሰኘው ድራማው ከቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የእጃቸውን ሰዓት እንዲቀበል አበቃው። ይህንኑ በማመላከት «ድርሰት መጻፍ የጀመርሁት በልጅነት ቢሆንም የመጀመሪያውን ገቢ ያገኘሁት ግን በ 13 ዓመቴ በ1941 ዓ.ም. አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ሳለሁ ንጉሡ እምቦን ሲጐበኙ ባቀረብሁት ትያትር ነው። ገቢውም በግምት 102 ብር ሲሆን ከዚያ ውስጥ የእኔ ድርሻ 8 ብር ነበር» በማለት የሎሬት ጸጋዬ የግል ማኅደር ይመሰክራል። በዚህ የተበረታታው አዳጊ ወጣት ጸጋዬ ከ16 እስከ 20 ዓመት /1944-48 ዓ.ም./ በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በነበረው ቈይታ «የሕይወት መሥዋዕት /ስለ ኢጣሊያን የሚያወሳ/፣ የደም አዝመራ፣ የዕድገት መሥዋዕት፣ እኔም አዳም ነኝ/ ስለ ጐሳ ልዩነት የሚተርክ/ እና ወይዘሮ እና ዓለም» የተሰኙ ተውኔቶችን በመጻፍ በማዘጋጃ ቤት፣ በወወክማና በተለያዩ ትምህርት ቤቶች አቀረበ። በዩኔስኮ አማካይነት የትምህርት ዕድል አግኝቶ ወደ እንግሊዝ ከመሄዱ ቀደም ብሎ በ1949 ዓ.ም. በ21 ዓመቱ «በልግ» እና «የእሾህ አክሊል» የተሰኙ ተውኔቶችን በመጻፍ በቀዳማዊ ኃ/ሥላሴ ቴአትር አቀረበ።

ገና በ13 ዓመቱ ጃንሆይ የሸለሙትና በአዲስ ዘመን ጋዜጣ በ13 ዓመት ደራሲ እንደ ሆነ የተጻፈለት ጸጋዬ እስከ ሕይወቱ ፍጻሜ የኖረው ሽልማት እየተከተለው ነበር። በ29 ዓመቱ የመጀመሪያው ወጣት የአማርኛ ሥነ ጽሑፍ የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ተሸላሚ ሆነ። ያኔ ግን አለቃው የነበሩት ሰው ያሉትን ምንጊዜም አይረሳውም፣ «አይ ጸጋዬ እንኳን ደስ ያለህ አልልህም ከእንግዲህ መከራ ገባህ እግዜር ያውጣህ» በማለት ቀሪውን የሕይወት ዘመኑን የተቃውሞ ትግል ተንበየውለት ነበር። በ1957 ዓ.ም. ከሀገር ውጪ በትያትር ምርምር ሥራም ከሴኔጋሉ ፕሬዘዳንት ሊዮ ፖል ሴዳት ሴንግጐር ከፍተኛ ድጋፍ ሲያገኝ *«Commander of the National Order of the Republic of Senegal»* ማዕረግ ተሸለመ። በአፍሪካ ባህላዊ ጥናት የሰው ልጅን ቅድመ ታሪክ አስመልክቶ «ክብረ አፍሪካ» የተሰኘ ጥናታዊ ሥራ በመሥራት ላት



ያለ የክብር ተሸላሚ፣ የኖርዌይ ደራስያን ማኅበር የክብር ተሸላሚ፣ ከቀዳማዊ ኃ/ሥላሴ የልጅ ልጅ ከልዑል ኤርምያስ ማህለ ሥላሴ የብላቴንነት ማዕረግ ተሿሚ ሲሆን ሌሎች በርካታ ሽልማቶችንም አግኝቷል። BBC Focus on Africa በጥርና በመጋቢት እ.አ.አ 1999 ዓ.ም ዕትም የአፍሪካ ታላላቆች በሚል ርዕስ በአውሮፓውያን አቈጣጠር በሁለት ሺህ እንማን ኮከብ ይሁኑ በሚል ለአንባብያን በቀረበው ጥያቄ መሠረት በጊዜው የግብጽ መሪ ከነበሩት ጀማል አብደልናስር፣ የደቡብ አፍሪካ ፕሬዝዳንት ከነበሩት ኔልሰን ማንዴላና ከሌሎችም ጋር የጸጋዬን ስምና ፎቶ ከነሥራቸው አስፍሮ ነበር። የጸጋዬ ስም በጸሐፌ ተውኔት፣ በባለቅኔዎች፣ በመካከለኛና ምስራቅ ዕውቅ ሰዎች፣ በአፍሪካ ዝነኛ ሰዎችና የዓለም አቀፍ «እነማን ምን ሠሩ» መጻሕፍት ላይ የሰፈረ ሲሆን ከ40 በላይ ትያትሮችን፣ ከ9 በላይ የምርምር ጽሑፎችን፣ በርካታ ግጥሞችና በርካታ የትርጉም ሥራዎችን ሠርቷል።

በ1970ዎቹ መጀመሪያም በኢትዮጵያ የባሕልና ስፖርት ሚኒስቴር በምክትል ሚኒስትርነት ማዕረግ ለተወሰነ ጊዜ አገለገለ። በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የትያትር ዲፓርትመንትም በረዳት ፕሮፌሰርነት በመሥራች ዲሬክተርነት ሠርቷል። የኢትዮጵያ የሰላም የአንድነትና የወዳጅነት ዋና ጸሐፊም ሆኖ አገልግሏል።

ጸጋዬን ልዩ ከሚያደርጉት ነገሮች ውስጥ አንዱ የሙያው በኅ ተጽዕኖ እዚሁ ዘንቦ እዚሁ የሚያባራ አለመሆኑ ነው። በአገሩ መንፈስ በአየሯ አብርሆ ተውኔት ጽፎ ለመድረክ ያበቃል፤ የታዳሚው ጥማት ትያትሩን ወዳላዩ ይጋባል፤ ድራማው መጽሐፍ ሆኖ ይታተማል፤ ጠረኑ ብዙ የአፍሪካ አገሮችን ያውድና የጸጋዬ ድራማዎች በየመድረካቸው ይታያሉ። ከዚያም አልፎ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ሥራዎቹ በአውሮጳና በምድረ አሜሪካ



ለመድረክ የበቁለት ሽንጠ ረጅም ብዕር የነበረው ጸሐፊ ነው። ከክምሩ ለመምዘዘም ያህል የምርምር ሥራው ውጤት የሆነው፣ «አርት ኢን ዘ ላይፍ ኦቭ ኢትዮጵያን ፒፕል»ን ያቀረበው



ዩኔስኮ በዳካር ሴኔጋል ባዘጋጀው የመጀመሪያው የዓለም ጥቍሮች የኪነ ጥበብ ፌስቲቫል ላይ ነበር። በተመሳሳይም የአፍሪካ አንድነት ድርጅት በአልጀርስ ባዘጋጀው ፌስቲቫልም ላይ ሲያቀርብ ዓለማቀፋዊውን አመለካከት ወደ ኢትዮጵያ፣ ኢትዮጵያዊ የኪነ ጥበብን ቅመም ደግሞ ወደ ዓለም ሲያቃምም እንዳንዶቹንም እየደጋገመ ከ 30 ወደ ሚበልጡ አገሮች ተጒዞአል። በጥቅሉ ለአንድ ኢዮቤልዩ ዓመት (አምሳ ዓመታት) የጥበብ ደንቃራ ጣልቃ ገብ ክሥተቶችን ሁሉ ተቋቁሞ በተለይም ለትምህርቱ ዓለም ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊ ባህልን፣ ሥነ ጽሑፍንና ኪነ ጥበብን በአዝልቆትና (Consistently) በስፋት ለዓለሙ አስተዋውቋል። ይህ ዘላቂ ጥረቱም ጸጋዬን ዓይነተኛ የባህል አስተጋባሪ ያደርገዋል።

ጸጋዬ ታሪካዊም ሆነ ዘመናዊ እንዲሁም ሼክስፒራዊ ተውኔቶችን ወደ አማርኛ ቋንቋ በመተርጎም ያቀረበልን ቢሆንም ለሕትመት የበቁ የተሳኩ የእንግሊዘኛ ሥነ ጽሑፎቹ ሁለት ብቻ (Oda Oak Oracle እና Collisions of Altars) ናቸው። ይሁን እንጂ እነዚህ የጸጋዬ የሥነ ጽሑፍ ሥራ ውጤቶች የእርሱን ብርቅዬ የሥነ ጽሑፍ ተሰጥዖ በሚገባ ያንጸባርቃሉ።

የአፍሪካውያንን ቅድመ ቅኝ አገዛዝና ድኅረ ቅኝ አገዛዝ ተሞክሮን በሚመለከት፣ እነዚህ ጽሑፎቹ ከሌሎች አፍሪካውያን ጸሓፍት የሥነ ጽሑፍ ሥራዎች ጋር የርእዮተ ዐለም ተመሣሣይነት ይንጸባረቅባቸዋል።

ጸጋዬ በሃይማኖታዊ ንጽረተ ዐለም፣ ማኅበረ ሰቡንና በውስጡ ያለውን የፖለቲካ ሥርዓት ሁሉ ይቃኛል። በዚህ ቅኝቱም ፍትሕ እኩልነትና የሰው ልጆች መብት ዋነኛ ጉዳዮቹ ናቸው። በተለይ ጥቁር አፍሪካ፣ ጥቁር መሬት፣ ሊላው ቀርቶ አማልክትን ሳይቀር በጥቁር ቀለም ማየትን ይመርጣል። በአንድ በኩል ይህ አፍሪካ ተኮር አመለካከቱ፡ በተለይ በአማልክትና በሰው ልጆች ታሪክ መካከል ከሚንጸባረቀው መስተጋብር አንጻር ሲታይ፣ ጸጋዬን፣ የራሱ የሆነ አፍሪካዊ



ነገረ መለኮት (African Theology) ያዳበረ ያስመስለዋል። የጕላ አፍሪካዊነትም ከሚንጸባረቅበት ምክንያቶች አንዱ ከዚህ አንጻር ነው። ኢትዮጵያ ግን ለጸጋዬ በተለየ መልኩ የልሳን ውበትና የቃል ኀይል ያለባት አገር ናት። ይህች አገር በሕዝቦች ስነ ቃልና ትረት የመጠቀች አገር ናት።

ገና በወጣትነቱ ከአማርኛ ቋንቋ ውጪ በእንግሊዝኛ ቋንቋም ትያትሮችንና ግጥሞችን የሚጽፈው ጸጋዬ ሥራዎቹ በተለያዩ የአፍሪካና የአውሮጳ እንዲሁም የአሜሪካ ግዛቶች ታይተውለታል። ከዚህም አንጻር «ቴዎድሮስ» «አዝማሪ»ና «የዋርካ ሥር ትንግርት» የተሰኙ ሥራዎቹን አቅርቧል። ሥራዎቹ ወደ ፈረንሳይኛ፣ ዴኒሽ ጣሊያንኛና ሮማንያኛ ተተርጕመው በእንግሊዝ፣ በዴንማርክ፣ በኢጣሊያ፣ በሩማንያ፣ በናይጄሪያ፣ በኬንያ፣ ታንዛኒያና አሜሪካ ለመታየት በቅተዋል።

በ1966 ዓ.ም. በኢትዮጵያ የተከሠተውን የፖለቲካ ለውጥ ተከትሎ ቀዳማዊ ኃ/ሥላሴ ቴአትር ይሰኝ የነበረው ወደ «የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቴአትር»ነት ተለወጠ። ጸጋዬም የዘውድ ሥርዓት ጥሎበት የነበረው እገዳ ተነሥቶለት ወደ ሙያው ተመለሰ። እንደ ተመለሰም «ሀሁ በስድስት ወር»የተሰኘውን ትያትር ለመድረክ አበቃ። ፕሮፌሰር ንጉሤ አየለ እንደሚሉት ለጸጋዬ እነዚህ ዓመታት ለብሔራዊ ቴአትር ግት ጥበቡን ያንቈረቈረበትና አሳዳጊ ሞግዚትነቱን የተወጣባቸው ዓመታት ናቸው።

ወደ ሥራው እንደ ተመለሰም አስቀድመው ጨቋኝት ያስሙለት የሙያ ባልደረቦቹ ስለ ነበሩ ከላይ ከተጠቀሰው ቴያትር ያገኘውን ገቢ ለሥራቸው ለሚያስፈልጋቸው ባለ ሙያዎች እና የቲአትር ጥበብ ፍቅር ያላቸውን ወጣቶች ለማሠልጠኛ ለታሰበው «ሀሁ ስቱዲዮ» ግንባታ እንዲውል ሰጠ። ከፊሉን ደግሞ በብሔራዊ ቴአትር ቅጥር መናፈሻ ውስጥ ላለውና «ለንቃት ተራማጅ ባላገር» በመባል ለተሰየመው ሐውልት ማሠሪያ አዋለ። መምህር አሰፋ ወርቁ «ጋሽ ጸጋዬ የትያትር ታሪክ በኢትዮጵያ ዘመናዊውን ፈለግ





እንዲከተል የመጀመሪያውን ትምህርት ቤት ‹ሀሁ ስቱዲዮ›ን ያቋቋመልን ነው» በማለት ይናገራል ። ሎሬት ጸጋዬ ብሔራዊ ቴአትር ቅጥር ግቢ ውስጥ ስለ ቆመው ሐውልት ሲናገርም «...ሐውልቱ ለእኔ የአፍሪካዊነት ሰብእና የመንፈስ ኵራት ተምሳሌት ነው ብሏል።»

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቴአትር ዲሬክተር ሆኖ በመሥራት ላይ ሳለ በባህልና ስፖርት ሚኒስቴር በምክትል ሚኒስትርነት የቋሚ ተጠሪነት ሹመት በማግኘት ሠርቷል። ሆኖም ከሕዝብ ጐን የሚቆመውና ኪነ ጥበባዊ እውነትን የሚገልጸው ጸጋዬ ቢሮክራሲያዊ አሠራር ሳይመቸው ቀርቶ እስከ መታሰር የሚያደርስ ብዙ ዋጋ ከፈለ። ለጸጋዬ ጽናት እናቱ ናት፤ በሷ ጥበብን ይጨምቃል። ስለዚህ ማስፈራራት፣ በተፈላጊዎች ጥቁር መዝገብ ውስጥ መግባት፣ መታሰር፣ መከርቸም ወዘተ የጥበብ ጥብትናውንና ትንግርት የሚያሰኝ አይሸነፌነቱን አልነኩበትም። እንዲያውም ጸጋዬ ስለ እውነት ዋጋ ለመክፈል ያለው ዝግጁነት የደፋርነቱን ልክ እንደሚያሳይ ዶ/ር ንጉሤ ተፈራ[5] ሲናገሩ፦

> በደርግ ዘመን ከኢ.ሠ.ፓ.አ.ኮ. ጽ/ቤት በተሰጠ ትእዛዝ መሠረት፣ ሙስናን ለማስወገድ የኪነ ጥበብ ባለሙያዎች ከቁጥጥር ኮሚሽን ጋር በመሆን፣ የሙያቸውን ሚና እንዲጫወቱ ተጠይቀው ወደ ጽ/ቤቱ ከተጠሩት ሰዎች መካከል፣ አንዱ ጸጋዬ ገብረ መድኅን ነበር። ጸጋዬ በስብሰባው ላይ የሰጠው አስተያየት እንዲህ የሚል ነበር፤ 'እናንተ እኮ እኛን ሌባ ሻይ [ሌባ አፈላላጊ] አደረጋችሁን፣ ችግሩ ግን ሌባ ሻዩን የሚሰደው ሌባው መሆኑ ነው።' በማለት ጸጋዬ ነገሩን ገለበጠው። የነበረው አመራር ራሱ ያለበትን ሁኔታ ከእውነት ጋር አለማመሳከሩን ፊት ለፊት በመናገር 'እውነተኛ መሆናቸውን የማውቀው ከእነርሱ ሲጀምር ነው'

በማለት ለእውነት ያሳየውን ጽኑ አቋም ዶ/ንጉሤ ገልጸዋል።



[5] Population Media Center (PMC) Ethiopia, Country Representative

ከእስር ከተፈታ በኋላ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የቴያትር ጥበብ ትምህርት ዘርፍ በረዳት ፕሮፌሰርነት ማእረግ የዛሬውን የትያአትር ጥበባት ትምህርት ክፍል እንዲመሠረት በማድረግ ተቋሙን በዲሬክተረነትና በአስተማሪነት ያገለግል ጀመር። የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የትያትር ትምህርት ክፍል ሊቀ መንበር የሆኑት መምህር አሰፋ ወርቁ ስለ ጸጋዬ በአንድ ወቅት ሲናገሩ፣ «ሀሁ በስድስት ወር፣ አቡጊዳ ቀይሶን፣ መልእክተ ወዛደርን ... [በመሳሰሉ] ሥራዎች በአገራችን ለመጀመሪያ ጊዜ አዲስ የትያትር አጻጻፍ ስልትን ያስተዋወቀልን ነው» ብለው ነበር።

ጸጋዬ ከመድረክ በታገደባቸው አራት ዓመታት ማለትም 1963 እስከ የካቲት 1966 ዓ.ም. ምናቡን በማስፋትና መንፈሱን በማጠንከር የአፍሪካን ቅድመ ታሪክ የቴያትርና የጥበባት ሥልጣኔ በተማሪነት ደረጃ በተለያዩ አገራት በመዘዋወር ሲያጠና ቈየ። በዚያ ቈይታውም «ጥበብ በኢትዮጵያ ሕዝብ ዙርያ፣ የካም የጥቍር ሕዝቦች፣ በግብጻውያን ቴያትርና አፍሪካ ለጥንታዊ የግሪክ ቴአትር ባህል መነሻ፣ ክብረ አፍሪካ በዓለም ውስጥ፣ የዓለም የነገደ አክሱስ ከተማና፣ የመጀመሪያው ተዋናይ» የተባሉ የምርምር ውጤቶችን በማዘጋጀት ለኅትመት አበቃ። በማስታወሻው እንዳሰፈረው እነዚህን የምርምር ሥራዎች ለማዘጋጀት ባደረገው ጕዞ በጊዜው የነበሩት የሴኔጋል ፕሬዝዳንት ሌዎፖልድ ሴዳር ሴንጐር ድጋፍ ይህ ነው የማይባል እንደ ነበር ጠቅሷል። በተለይ 1965 ዓ.ም. መጻረሻና በጥቅምት 1966 ዓ.ም. መጀመሪያ ላይ ከተማሪነት አበሉ አጠረቃቅሞ «እሳት ወይ አበባ» የተሰኘ የግጥም መድብል ለሕትመት ሲያዘጋጅ ፕሬዝዳንት ሊዎፖልድ ሴዳር ሴንጐር ለእሳቤው መሳካት የተጫወቱት ሚና ከፍ ያለ እንደ ነበር ጸጋዬ በማስታወሻው ጠቅሷል። «እሳት ወይ አበባ» ብቸኛው የሎሬት ጸጋዬ የግጥም መድበል ሲሆን ከ1951 እስከ 1965 ዓ.ም. ባሉት 14 ዓመታት የጻፋቸውን ግጥሞች ያካተተበት ነው።



ይህ የግጥም መድበል መጀመሪያ



በ1966 ዓ.ም. ታተመ። ቀጥሎም ከ33 ዓመታት በኋላ በ1999 ዓ.ም. ቤተሰቦቹ ለሁለተኛ ጊዜ ለሕትመት ያበቁት ሲሆን አሁን ደግሞ ይህ የጸጋዬ የሕይወት ውልብታ በተጻፈበት ጊዜ መጽሐፉ በሲዲና በካሴት ተደግፎ በራሱ በሎሬት ጸጋዬ ድምጽ ተነበ ለተደራስያን ቀርቧል። በ1999 ዓ.ም. በታተመው መጽሐፍ የጀርባ ሽፋን ላይ ፕሮፌሰር ንጉሤ አየለ የሰጡት አስተያየት እንደሚከተለው ይነበባል፦

> ብላቴን ጌታ ጸጋዬ ገብረ- መድኅን በዚህች ዓለም በኖረበት አጭር ዕድሜው በተለያዩ የዕውቀት ዘርፎች አያሌ አስተዋጽኦ ያበረከተ ልዩና ሕያው የኢትዮጵያ ዋርካ ነው። እሳት ወይ አበባ በሚል ርእስ በ1966 ዓ.ም. የታተመው ይህ የብላቴን ጸጋዬ መድበለ ግጥም በ21 ገጾች ውስጥ የተካተተና ከወልዲያ እስከ ድሬደዋ፣ ከለንደን እስከ ዳሬሰላም ባሉ ቀዬዎች የተንቈረቈረ 52 ግጥሞቹን ያካተተ ጥራዝ ነው። እነዚህ ጽሑፎች የብላቴን ጌታ ጸጋዬን ስጦታ፣ ጥበብና ቅኔ ከብዙ በጥቂቱ የሚያንጸባርቁ ብርቅዬ ሥራዎች ናቸው። «የብርዕ ወገናዊነት ምንግዜም ለሕዝብ ነው» ያለውን ሐቅ የብርዕ አርበኛው ጸጋዬ እንጸባርቆታል። «እሳት ወይ አበባ» የኢትዮጵያን ገጸ ምድር የሚዳስስ የኢትዮጵያውያንን የልብ ትርታ የሚያስተጋባ ባህላዊ ገጽታን የሚያፍታታ ጥራዝ ነው።

ጸጋዬ ዕድሜው እየገፋ ሲመጣ አሳቡም እየንለበተ ይመጣል። የብርዕ ቾሩፋቱም የብስለት እድገት እንደዚያው ከቤተ ሰባዊ ታሪክ ወደ ማኅበረ ሰባዊ ፣ ከማኅበረ ሰባዊ ፣ ወደ አገራዊ ፣ ከአገራዊ ታሪክ ወደ አህጉራዊ ፣ከአህጉራዊም የሥነ ሰብ (Anthropology) ጥናት አደገ። በእንዲህ ዓይነቱ ኪነ ጥበብን ባካለለ ሁኔታ የተሰባጠረ የዕውቀት መስክ የሰፈፈ. ቢሆንም «ሳይምታታብኝ እንዲያውም የእንጻ መብራት ለእንጻ ፍለጋ ጠቅሞኝ ስውሩን አግኝቼበታለሁ» ይላል። ጸጋዬ በውደ ጥበባዊ አእምሮ፣ ዓለም አቀፋዊ ልብ ውስጣዊ ጕልበት ለማግኘት አይነጥፌ ጸሓፊም ለመሆን የበቃው ለዚህ ነው ።



ከሥርዓት ሥርዓት ሲለዋወጥ የተሰማውን፣ ያየውንና የተገነዘበውን ከመጻፍ ወደ ኋላ የማይለው ጸጋዬ ሁለተኛው የሥርዓት ለውጥ ሲከሰት ፈጣን የለውጥ አርበኛ በመሆን ከ«ሀሁ በስድስት» ወር የቀጠለውን «ሀሁ ወይም ፐፑ» ፖለቲካዊ ትያትር አቀረበ። በወቅቱ የትያትሩ አዘጋጅ የነበረው አርቲስት ዓለሙ ገብረ አብ የሆነውን ሁኔታ ሲገልጽ፦

> ሀሁ ወይም ፐፑን ጽፎ እንሥራው ሲለኝ በቴአትር ቤት እንደማያሠሩን ሰውቀን ወጣቶቹን አርቲስቶች እነ ተስፋዬ ሲማ፣ ውሂበ ሥላሴና ሌሎቹንም ሰብስበን በንግድ ሥራ ኮሌጅ አዳራሽ ተለማመድን። ከዚያ ሚኒስትሩን አስፈቅዶ ወደ ብሔራዊ ቴአትር አዳራሽ አመጣነው። ከዚያ በፊት በልምምድ ላይ እያለን 'ጸጋዬ የሆነ ቴአትር ጽፎ ዓለሙ ገብረ አብ ሕፃናት ሰብስቦ እያንጫጫ ነው' ተብሎ ተወራብን። ትያትሩ እንደ ተከፈተ የሕዝብ ጎርፍ ሆነ። በሕይወቴ የሚያስደስተኝ የጸጋዬን ትያትሮች መጫወቴና የመጨረሻ ተውኔቱን ማዘጋጀቴ ነው ...።

ሎሬት ጸጋዬ ከወ/ሮ ላቀች ሦስት ልጆችን አፍርቷል። የመጀመሪያዋ ወ/ሮ ዮዲት ጸጋዬ በሙያዋ የስነ ሰብ ጥናትን ያጠናችና በሴቶች መብት ማስከበር ጉዳይ ላይ ያተኮረች ፣ መካከለኛዋ ወ/ሮ ማህሌት ጸጋዬ የኮሙኒኬሽን ባለ ሙያና ዶ/ር ዓደይ ጸጋዬ የህክምና ባለሙያ ሲሆኑ ሁሉም አሜሪካ የሚኖሩ ናቸው። የልጅ ልጅ ለማየትም ታድሏል። ከ1980ዎቹ መጨረሻ ጀምሮ ከኢትዮጵያ የወጣው ጸጋዬ በኩላሊት ሕመም በከፍተኛ ሁኔታ ይሠቃይ ጀመር። ሕመሙም እየጠናበተ ስለ ሄደ በኒውዮርክ ቅዱስ ባርናባስ ሆስፒታል የኩላሊት ሕክምና ማእከል ሲታከም ቆይቶ ለ70 ዓመት መባቻ 69 ዓመት ከ11 ወር ላይ ለትውልድ ቋሚ ሥራ ሠርቶ ከነድምቀቱ ከዚህ ዓለም በሞት ተለየ። የካቲት 1998 ዓ.ም. አስክሬኑ ከአሜሪካ መጥቶ ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን ሥርዓተ ቀብሩ ተፈጽሟል። እግዚአብሔር እንደ ጸጋዬ ያሉ ፣ ሌላ ጠቢባን፣ ሌላ ደማቆች ይስጠን !






ጥበብ ይናፍቀኛል
ተቻችሎ የሚኖር ሕዝብ ያስቀናኛል
ድንቁርና ያስፈራኛል
ጦርነት ያስጠላኛል

<u>መወድስ</u>

**ማኅደረ ሼክስፔር ትምክህተ አፍሪካ**
**አንተ ቀድመህ ብትሄድ ቅኔህ መች ተነካ**
**የጥቁሮች አኪር የጥበብ ዕቃ**
**ጸጋዬ ረቂቅ የብዕር ላንቃ**

## <u>ትምህርተ ውልብታ</u>

**የትውልድ ዘር፣ የእድገት ሥፍራ፣ የትምህርትና የሕይወት ተመክሮ ፣ለብሔራዊ፣ ለአህጉራዊ ብሎም ለዓለም አቀፋዊ የሰው ልጆች ሁለእንተናዊ እድገት የሚያመጣው አስተዋጽኦ ከፍተኛ ነው።**

**ስለ እውነት በብርዕ ከመናገርም አልፎ በአደባባይ ዋጋ ለመክፈልም ተዘጋጅቶ መናገር የእውነተኛ ስብእና መታያ ነው።**



## የውልብታ ምንጭ


Molvaer, Reidulf K., *Black Lions: The Creative Lives of Modern Ethiopia's Literary Giants and Pioneers,* Lawrenceville: The Red Sea Press, Inc., 1997

Tadedesse Adera and Ali Jimale Ahmed, (Eds) *Silence is not Golden: a critical anthology of Ethiopian Literature,* (Biodun Jeyifo, Art and Ideology in the Plays of Tsegaye Gebre-Medhin) The Red Sea Press Inc., 1995

ጸጋዬ ገብረ መድኅን እሳት ወይ አበባ መጽሐፍ 1999 የጀርባ ሽፋን

ኀሊና መጽሔት ነሐሴ 1984 ገጽ 8

ኢትኦጵ ጋዜጣ ሐምሌ 1997 ገጽ 13

ጦቢያ መጽሔት የካቲት 1997 ገጽ 8

ለዛ መጽሔት ቁ 2 መስከረም 1985 ገጽ 8- 13

ሕሊና መጽሔት ነሐሴ 1984 ገጽ 6

ሙያችን መጽሔት 1999 ገጽ 36

ቃለ መጠይቅ ከዶ/ር ንጉሤ ተፈራ ጋር ነሐሴ 1999

ቃለ መጠይቅ ከአቶ አሰፋው ዳምጤ ጋር መጋቢት 3፣ የንቲት 26 1999

ቃለ መጠይቅ ከዓለሙ ገብረ አብ የካቲት 1999

በየካቲት 1998 በኢትዮጵያ ብሔራዊ ቴአትር ዝክረ ጸጋዬ ገ/መድኅን ዝግጅት ላይ አቶ አሰፋ ወርቁ የተናገሩት

Negussay Ayele (Professor) www.ethiopians.com/tsegaye/







## የአንባቢው የግል ማስታወሻ












# ፲፪



## በዓሉ ግርማ

## 1931–1975

## ሰማዕት ብርዕ

*ደራሲ የአማልክትን ባሕርይ ይጋራል። ይህን ባሕርይ የሚጋራውም የኀብረተ ሰቡ ሻማ ሆኖ እየበራ፣ በደስታ እየነደደና ራሱ በደስታው እሳት ውስጥ እየተቃጠለ ነዶ ሲያልቅ ብቻ ነው።*

«እንባ እንባ ይለኛል
ይተናነቀኛል፤
ግን እንባ ከየት አባቱ!
ደርቋል ከረጢቱ
ሣቅ ሣቅም ይለኛል
ሥቆ ላይስቅ ጥርሴ፤
ሥቃ እያለቀሰች መከረኛ ነፍሴ።»

በዓሉ ግርማ

ለማንባት እየተፈለገ የእንባ ከረጢት ሲነጥፍ፣ መተናፈሻ የሌለው የስሜት እብጠት ይፈጥራልና ማልቀስ መቻል ቀላል ነገር አይሆንም። ከባዱ ነገር ማልቀስ አለመቻል ነው። ደግሞ መሣቅ እንፈልጋለን። ሆኖም ግን ጥርሳችን አይሥቅም፤ እውነተኛውን የደስታ ስሜት አያበሥርም። ለምን? ጥርስ ውበት ያለው ሣቅ የሚያመነጨው በማያለቅስ ነፍስ ሲታዘዝ ነው። ሥቆ የሚያለቅስ "መከረኛ" ነፍስ ካለ፣ ሣቅ የለም፤ እንባም የለም።

እርሱ የብዙኃንን እንባ ለማንባት የፈለገ ቢሆንም። የነፍሱ ሥቃይ ሣቁን ሸሽጎበት ኖሯል። ይህ ሰው በሕይወት በቈየበት አጭር ዘመን ረዥምና አንጸባራቂ ታሪክ ትቶ አልፏል። በጋዜጠኝነት ሙያው ደራሲ ሆኖ መፈጠሩን በመግንዘቡም ትቶ ያለፈው ታሪክ የሐቅ እና የኅሊናዊ ነጻነት ዐምድ ሆኗል።



«ሕንድንና ኢሉባቡርን ምን ያገናኛቸዋል?» ቢባል ምላሻችን ይኸው በዓሉ ግርማ ነው፣ ይሆናል። እንዴት የሚል ጠያቂ ከመጣ ደግሞ አናጢው ባቡ ከሕንድ ጉጅራት ግዛት መጥተው ከኢሉባቡሯ ኦሮሞ ከወ/ሮ ያደኒ ዳባ የቀለም ቋቱን በዓሉን በወርሃ መስከረም 1931 ዓ.ም. በመውለዳቸው ነዋ! የሚል መልስ እንሰጣለን።[1] እትብቱ ከተቀበረበትና አፍላ የልጅነት ዕድሜውን ካሳለፈበት ከኢሉባቡር «ሱጴ ቦሮ» መንደር በመልቀቅ ወደ አዲስ አበባ ሲመጣ የዘጠኝ ዓመት ልጅ ነበር። በዓሉ ወደ አዲስ አበባ ከመምጣቱ በፊት አለቃ ዳዊት በሚባሉ መምህር አማካይነት ከፊደል ቈጠራ እስከ ዳዊት ድረስ ያለውን ትምህርት ዘልቋል። ከአንደኛ እስከ አራተኛ ክፍል የተማረው «ከአድማስ ባሻገር» በተሰኘው ልብ ወለድ መጽሐፉ መልክአ ምድሯን ቁልጭ አድርጎ ባሰፈራት በዚያችው በ«ሱጴ ቦሮ» መንደር ነው። ከዚያ በኋላ ግን አሳዳጊውና ስመ አባት መጠሪያው አቶ ግርማ ወደ አዲስ አበባ ካመጡት በኋላ የመለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን በልዕልት ዘነበ ወርቅ ትምህርት ቤት በአዳሪ ተማሪነት የተከታተለው በዓሉ፣ በ1951 ዓ.ም. ፊተና አልፎ ወደ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ከመግባቱ አስቀድሞ የ2ኛ ደረጃ ትምህርቱን በጀነራል ዊንጌት ትምህርት ቤት አጠናቀቀ።

---

[1] Molvaer, Reidulf K., *Black Lions: The Creative Lives of Modern Ethiopia's Literary Giants and Pioneers*, Lawrenceville: The Red Sea Press, Inc., 1997 342 ጋዜጠኛና ደራሲ በዓሉ የሚጠራው ከአፍላነቱ ዕድሜ ጀምሮ ባሳደጉት በአቶ ግርማ ወልዴ ስም ቢሆንም፤ ወላጅ አባቱ ሕንዳዊ አናጺና በትውልድ አገራቸውም የቤተሰብ ኃላፊ የነበሩ ሰው መሆናቸውን የ"ብላክ ላየን" መጽሐፍ አዘጋጅ ጽፏል። በዓሉ የመንግሥት ባለ ሥልጣን በነበረበት ጊዜም ለሥራ ጉዳይ ወደ ሀገረ-ሕንድ ሲያቀና "ጉጅራት" በተባለው የሀገሪቱ ግዛት ይኖራሉ ስለተባሉት ወላጅ አባቱ ለማወቅ ያልተሳካ ሙከራ ማድረጉንም "ሬዱልፍ.ኬ.ሞልቬር" በመጽሐፉ አስነብቧል። በዓሉ ግርማን ያፈሩትና "ባቡ" ወይም "ጀርማንዳስ" ተብለው የሚጠሩት ሕንዳዊ ከኢትዮጵያ ወደ አገራቸው የተመለሱት ከቤት ሰባቸው ለመቀላቀል በነበራቸው ፍላጎት የተነሳ መሆኑን አትቷል። በዚህም መሰረት በዓሉ ያደገው፣ የተማረውና እውቅ የሥነ-ጽሑፍ ሰው ለመሆን የበቃው፤ የሕንዳዊ አባቱ ጓደኛ ከነበሩት ከአቶ ግርማ ወልዴና ከባለቤታቸው ከወ/ሮ አምሳለ እንደሻው ቤተ ሰብ ጋር ከ"ጐሬ" ወደ አዲስ አበባ ከመጣበትና አብሮ መኖር ከጀመረበት ጊዜ ወዲህ ነው።

የሁለተኛ ደረጃ ተማሪ በነበረበት ጊዜ በአማርኛም ሆነ በእንግሊዝኛ ቋንቋ ከተጻፉ ሥነ ጽሑፎች ጋር መተዋወቅ ጀመረ። በቋንቋ መምህሮቹ ዕገዛ በአጫጭር ሀረፍተ ነገሮች ሐሳብን የመግለጽ ስልትን፣ ለምንባብ የበቁ ጽሑፎችን የማንበብ፣ የመገምገምና የመተቸት ብቃትን ተካነ። አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ከገባ በኋላ በመጀመሪያዎቹ ሁለት ዓመታት የሥነ መንግሥት (ፖለቲካ) ሳይንስን ከጋዜጠኝነት ሙያ ጋር አጠና። ከትምህርት መቅሰም ሂደቱ በተጓዳኝም ለኢትዮጵያ ሔራልድ ጋዜጣ እንደዚሁም ለኢትዮጵያ ሬድዮ ዜና አቀባይ ሆነ። ከዚህም ባሻገር በዓሉ ግርማ፤ የ "ቪውስ እና ኒውስ" ጆርናል አዘጋጅ፣ በአ.አ.ዩ. የተማሪዎች ማኅበር ግንዘብ ያዥና የመረጃ ዘርፍ ኀላፊም ሆኖ አገልግሏል።

በ1960 ዓ.ም. ከቀዳማዊ ኃ/ሥላሴ ሥርዓት ጋር በመጋጨቱ ምክንያት ለ6 ወራት ያለ መደበኛ ሥራ ቆይቶ የነበረው በዓሉ፣ የአዲስ ዘመን ጋዜጣ ባልደረባ በነበረበት ወቅት (ቅድመ አብዮት 1966 ዓ.ም.) በኢትዮጵያ አብዮታዊ ለውጥ መከሠቱ አይቀሬ የመሆኑን ጉዳይ ያመላከተበትን "ከአድማስ ባሻገር" እና "የኀሊና ደወል" የተሰኙ መጻሕፍቱን ማሳተም ችሏል። እስከ 1967 ዓ.ም. "መነን" እና "አዲስ ሪፖርተር" የተሰኙት መጽሔቶች ዝግጅት ክፍል ባልደረባ የነበረው ይህ ባለ ታሪክ፣ የኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት የበላይ ኀላፊ በመሆን የሥራ አመራር ብቃቱን አስመስክሯል።

በዓሉ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ቈይታው በኋላ ወደ አሜሪካ በመጓዝ ከሚቺጋን ስቴት ዩኒቨርሲቲ በኮሙኒኬሽን ትምህርት የማስተርስ ዲግሪውን አግኝቷል። ከአሜሪካ እንደተመለሰም በማስታወቂያ ሚኒስቴር መስሪያ ቤት የጋዜጣና መጽሔቶች አዘጋጅ ከመሆን ጀምሮ እስከ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ቋሚ ተጠሪነት ድረስ ባሉት የኀላፊነት እርከኖች ሠርቷል። የበዓሉ የሕይወት ዘመን አገልግሎት ቆይታው ማስታወቂያ ሚኒስቴር መስሪያ ቤት ነው ማለት ይቻላል።





በ1957 ዓ.ም. ከወ/ሮ አልማዝ አበራ ጋር ትዳር የመሠረተውና ክብረ በዓሉ፣ ዘላለም በዓሉና መስከረም በዓሉ የተባሉ የሁለት ወንዶችና የአንዲት ሴት ልጅ አባት ለመሆን የበቃው በዓሉ ግርማ፦ "ከአድማስ ባሻገር"፣ "የኀሊና ደውል"፣ "ደራሲው"፣"ሐዲስ"፣ "የቀይ ኮከብ ጥሪ"፣ "ኦሮማይ" የተሰኙትን ስድስት ተወዳጅ መጻሕፍት ለሥነ ጽሑፍ አፍቃሪያን አቅርቧል። በእነዚህም መጻሕፍት ልዩ የአጻጻፍ ዘዴውን በሚገባ አሳይቷል።

"ደራሲ የአማልክትን ባሕርይ ይጋራል። ይህን ባሕርይ የሚጋራውም የኀብረተ ሰቡ ሻማ ሆኖ እየበራ፣ በደስታ እየነደደና ራሱ በደስታው እሳት ውስጥ እየተቃጠለ ነዶ ሲያልቅ ብቻ ነው" የሚለን በዓሉ፣ በዚሁ ጉዳና ለማለፉ ሥራዎቹ ሕያው ምስክሮች ናቸው። "ኦሮማይ" በተሰኘው መጽሐፉ ምክንያት ታፍኖ የቀረው በዓሉ ግርማ በ"የቀይ ኮከብ ጥሪ" መጽሐፉ ውስጥ በሕይወት ዘመኑ የሚጠላው ነገር "ሳንሱር" የተባለውን ቅድመ ኅትመት ቊጥጥር እንደ ነበር፦ "እምአእላፍ" የተሰኘውን ስያሜ በሰጠው ገጸ ባሕርይ አማካይነት ግልጽ አድርጓል።

በዓሉ መሳጭና አርኪ በሆነ ብርዕ ነበር ገጸ ባሕርዩውን የሚያናግረው፣ ወይም ደግሞ በነፍሱ ውስጥ የነበረውንና "ሳንሱር"ን የሚኮንነውን ሐሳብ የሚዘራው ... "የወላጆች ቊጥጥር፣ የትምህርት ቤት ቊጥጥር፣ የመ/ቤት ቊጥጥር፣ የሚስትና የቤተሰብ ቊጥጥር፣ የህብረተሰቡ ቊጥጥር! መቼ ነው የሰው ልጅ የአስተሳሰብ ነጻነት የሚኖረው? በማለት ነበር። በርግጥ ይህ ሰው ስለ ራሱ፣ ስለ ማኅበረሰቡና በተለይም ስለ አገሩ መጪ ዕድል ቀድሞ ያወቀ "ነቢይ" አልነበረም ማለት ይቻላልን?

ይህ ባለ ታሪክ በብርዑ፦ "ቾኩያለሁ። የምንጠለጠልበት ገመድ ተዘጋጅቶ ይጠብቀኛል ... ለመኖር አልቻልሁም። ያለ ድርሰት ሌላ ሕይወት የለኝም። ምኞቴ በድርሰት ለሰው ልጅ ደስታን ማስገኘት ነበር። ግን ለሰው ልጅ ደስታ ለመስጠት አልቻልሁም። ለራሴም ደስታ አላገኘሁም።



ስለዚህ የመኖር ትርጉም አልታየኝም። ባዶነት ይሰማኛል። ባዶነትን ፍጹም የሚያደርገው ደግሞ ሞት ነው።..." ብሎ ነበር። ያለውም አልቀረ በ"ኦሮማይ" ወደ "ፍጹምነት" ተሸጋግሯል። በደራሲነቱ አድርባይ መሆን አልቻለምና።

በዓሉ ግርማ፤ ይህን በመሰለው እምነትና መንፈስ፣ እውነትንና ሐቅን ብቻ ለመስበክ በምትታትረው ብርዑ ምክንያት ከተዘጋጀለት "ገመድ" ጋር በድፍረት ተገናኘ። የማኅበረ ሰቡን የአመለካከት ውልቃት ወደ ነበረበት ትክክለኛ ቦታ ለመመለስ ባደረገው ጥረት ከመንገድ ቀረ። ነገር ግን እውነት በምታብብበት፣ በምታፈራበትና ጣፋጭ ፍሬዋም በሚኮመራበት ... ቦታና ጊዜ ሁሉ ይኖራል። የነደደው ሡሸት ባጨለመው የሕይወት መድረክ ላይ ብርሃን ለመስጠት ነው።

"ጳጉሜ 5 ቀን 1975 ዓ.ም." በዓሉ ግርማ ለተሚገተሳት ሐቅ ዋጋ ሊከፍል ከሥራው ተሰናበተ። "የካቲት 24 ቀን በዕለተ ኀሙስ ከቀኑ በ11 ሰዓት" ውድ ባለቤቱ ወይዘሮ አልማዝ ነፍሷ ነግራት ኖሮ በዓሉ ያቺን የመጨረሻ ሰዓት ያለ ስንብት ከቤት ሲወጣ በኀይል የተቃወመችው ቢሆንም ዕጣው ግን እደጅ ሆና ትጠራው ነበር።

ስለ እውነት ሲሚገት የኖረውና "መቼ ነው የሰው ልጅ የአስተሳሰብ ነጻነት የሚኖረው?" የሚለውን የሃቅ ጥያቄ ያጉላው በዓሉ ግርማ፣ በ "ኦሮማይ" ኦሮማይ! ሆነ "ሴላቪ"!

ይህ ጋዜጠኛና ደራሲ ለኢትዮጵያ ማኅበረ ሰብ ብቻ ሳይሆን ለመላው የሰው ልጅ በጎ አመለካከት ነበረው። በዓሉ ሌሊትና ቀን የደከመበት ያልታተመ ሥራ ነበረው። ይሁን እንጂ ይህን ያልታተመ ሥራ ግን እሱ ቀደመ። ያልታተመው መጽሐፍ የሚያወሳው በሰዎች ላይ ስለሚፈጸም ግድያና ስለሚዋልባቸው ግፍ ... ነበር ። በዓሉ እንደተናገረው "ሰዎች ሥጋዬን ነው እንጂ ነፍሴን ምንም ሊያደርጓት አይችሉም ..." ይል ነበር።





"ከጕራው ዘልቄ እስኪ ልነጋገር
ካለ ሰው ቢወዱት ምን ያደርጋል አገር?
የኔ ውብ ከተማ
ሕንፃ መች ሆነና የድንጋይ አጥር
የኔውስ ከተማ የኔ ውብ አገር
የሰው ልጅ ልብ ነው
የሌለው ዳርቻ የሌለው ድንበር"·

ለበዓሉ ግርማ የደስታ መናኸሪያ የሆነው "ውብ ከተማ" የሰው ልጆች ንጹሕ "ልብ" ነበር። ከዚህም አልፎ በሥነ ጽሑፍ ሥራውም የሄምንግዌይ፣ የዶስቶዬቭስኪና የግራሃን ግሪን ተጽዕኖ ያረፈበት የእውነት ተሟጋች ጋዜጠኛና ደራሲ ሲሆን የዳኒሽ (Danish) ፈላስፋ የነበረው የሶረን ኪርክጋርድ /Soren Kierkegaard/ አድናቂ መሆኑም ይነገርለታል። ሃቀኛ፣ ደፋር እና የብርዕ አብዮተኛ ለመሆኑ በዓሉን በቅርብ የሚያውቁት ይመሰክራሉ።

አቶ አስፋው ዳምጤ ስለ በዓሉ ሲናገሩ፦ "በዓሉ ተስፋ የማይቈርጥና ምንጊዜም ረጋ ያለ ሰው ነበር። ዓለም በቁጥጥሩ ሥር ያለች መስሎ የሚሰማውና በጣም የሰከነ መንፈስ ያለው፣ በአለባበሱም ሆነ በአነጋገሩ አዋቂነቱ የሚገለጽ አይነት ሰው ነበር። በውስጡ የሚናወጠውና የሚመላለሰው ስሜት ምን ሊሆን እንደሚችል መገመት ባይቻልም ችኩል ሆኖ አልተፈጠረም።" ብለዋል።

"የበዓሉ ግርማ አድናቂና የሥነ-ጽሑፋዊ አስተምህሮው ተከታይ ነኝ" የሚለው እንዳርጌ መስፍን "በዓሉ በሕይወት ቢኖር ከቀደሙት ሥራዎቹ እጅግ በጣም የሚልቁ ድርሰቶችን ያስነብበን ነበር። በአካል አይቼው የማላውቀው ይህ ደራሲ በብርዕ በረከቶቹ አማካይነት የመንፈስ ወዳጄ እንድሆን አስገድዶኛል። ጊዜውንና ሕይወቱን ሰውቶ በተግባር በማስመስከሩ ትክክለኛና እውነተኛ ደራሲ ነበር። ትልቅ ባለሥልጣን ሆኖ ሳለ አብዛኛውን ጊዜውን ያዋለው በድርሰት ሥራ ላይ ነው። እንደዚህ ባይሆን ኖሮ በሚኒስቴር ማዕረግ ተቀምጦ ዛሬ



የእርሱ ሐውልት ሆነው የሚታዩትን ድንቅ መጽሐፎች ባልተወልን ነበር። ኃይል ያላቸውን ቋንቋዎች የድርሰቱ ማዋዣ የሚያደርገው በዓሉ፤ ቋንቋዎቹን ለአንባቢያን የሚያደርሰው በሥነ-ጽሑፋዊ ሥዕል ነው። አማላይና ስሜት ቆንጣጭ በሆኑ ሥዕላዊ ገለፃዎች የሚያስተላልፈው መልዕክትም ኃይል ያለውና ዕምቅ ነው። ለዚህም ነው በእያንዳንዱ የድርሰት ሥራው በመሪም ሆነ በአጋርነት የሚስላቸው ገፀ-ባሕርያትና ድርጊታቸው አይረሴ ሆነው ከአንባቢው ዘንድ የሚቀሩት።" አንዳርጌ አስተያየቱን በመቀጠልም፣ "የደራሲውን ፈጣንነት በተወሰኑ ጊዜያት 6 መጽሐፎችን ከማሳተሙ አኳያ ልናይ እንችላለን። በዓሉ ግርማ ፍቅርን በፍቅርነቱ፣ በቀልን በበቀልነቱ ... የማሳየት ችሎታ አለው። ተደራሲው የእሱን ሥራዎች 'የእኔው ገመናዎች ... ናቸው' ብሎ እንዲቀበል የማስገደድ አቅም ባለው መንገድ የሚጽፍ ነው። ይህ ቀለም አይቶ ትርጉም የመስጠት ክህሎት የነበረው ደራሲ፣ ሊነገርለት የሚገባ ታላቅ ጉዳይ ቢኖር እውነት ወዳድነቱ ነው። ሥልጣንና ገንዘብ እሱን የሚያማልሉት ሰው አለመሆኑ ነው። ኦሮማይ የተሰኘው ሥራው ለዚህ ምስክር ይሆናል። በዓሉ ማለት ሃቅ እና እውነት ከድርሰት ጋር ማለት ነው። የትም ተሸሽቶ፣ ምንግዜም ተፈርቶ የማይዘለቀውን እውነት፣ የማህበረሰቡን ሽሽግ ባህል ... የመግለጽ ችሎታ ነበረው። በኢትዮጵያ ሥነ-ጽሑፍ ታሪክ ላበረከተው ሃቅን በድፍረት የመግለጽ ባህል የመታሰቢያ ሃውልት ሊቆምለት ይገባ ነበር ..." ይላል።

"በሕይወት ቢቆይ ኖሮ በርካታ ጽሑፎችን ሊያስነብበን ይችል ነበር። በዓሉን ስናስብ ያጣነው ትልቅ ሰው፣ ትልቅ ጋዜጠኛ፣ ትልቅ የድርሰት ጥበበኛ፣ ትልቅ ባለሙያ ኢትዮጵያዊ መሆኑ ይሰማናል። አብሬው በነበርኩበት አጋጣሚ ሠርቶ ማሠራት የሚችል፣ የሰው ልጆች መብት እንዲከበር የሚታትር ሰው መሆኑን ተረድቻለሁ" የሚሉት አንጋፋው ጋዜጠኛ አቶ ይመኑ ይርዳው ናቸው።



በበዓሉ «ከአድማስ ባሻገር» መጽሐፍ ውስጥ፣ መሪ ገጸ ባሕሪው ጎ/ማሪያም ነው።



ጎ/ማሪያም በትራኪው መጀመሪያ ወደ መታጠቢያ ቤት ከመግባቱ በፊት ከሳሎኑ ቤት ውስጥ አልወጣ ብሎ ያስቸገረው ዝንብ፣ ድንገት መስኮቱን ሲከፍትለት ውልቅ ብሎ ወጣ። ይኼን ጊዜ ነበር በዓሉ በጎ/ማሪያም አንደበት ዝንቡን «አንተ መውጫ አገኘህ እኔ ግን መውጫ የለኝም» ብሎ የተናገረው።

የጎ/ማሪያም ቤት የሳሎን ዝንብ መስኮት ተከፍቶለት መውጫ አገኘ። ጎ/ማሪያምንም ዝንቡንም «የፈጠረው» በዓሉ መውጫ ቀዳዳ አጥቶ ታፍኖ ቀረ። ይህ ሁኔታ የሚቆጫቸው ኢትዮያውያን የሥነ ጽሑፍ ወዳጆች ብዙ ናቸው። ለአብነት ያህል ለ26 ዓመታት በሥነ ጽሑፍ መምህርነት ያገለገሉት አቶ ደርበው አዱኛ ከራሺያዊው እውቅ ደራሲ ከ ሶልዜንስቲን ጋር በማመሳሰል ቁጭታቸውን እንዲህ ይገልጻሉ ፦

> በዓሉ ግርማ እንደ ሊቪን ቶፍለር በመጽሐፎቹ የታወቀ ጋዜጠኛ ነበር። «ጋዜጠኛ ዝነኛ ደራሲ ሊሆን አይችልም» የሚለውን ያረጀ አስተሳሰብ ከሻሩ ጥቂት ጋዜጠኛ ደራሲዎች መካከል በዓሉ ግርማ አንዱ ነው። በዓሉ ግርማ ኦሮማይን ከጻፈ በኋላ በዚያው ወደ ሱዳን ቢሸሽ ኖሮ፣ እንደ አሌክሳንደር ሶልዜንስቴን ስንት መጻሕፍት በጻፈልን ነበር።

ደራሲ ማሞ ውድነህ በበኩላቸው፦ "በዓሉ ግርማ ከሰብዓዊነቱ፣ ከነበረው ሥነ-ጽሑፋዊ ዓላማ አኳያ መስዋዕት ሆኗል። መስዋዕት የሆነበትም ጉዳይ የኤርትራ ብሎም የኢትዮጵያ ችግር ነው። በብርዕ የደረሰበትንና የሚያውቀውን ሁኔታ የታሪኩ ባለቤት ለሆነው ሕዝብ ግልጽ አድርጓል። በዚህ ረገድ ዓርአያነቱ የጐላ ነው። ኦሮማይን ከኢትዮጵያ ውጪ ሆኖ ሊጽፈውና ሊያሳትመው ይችል ነበር። የመረጠው ግን እውነቱን ይዞ ማለፉን ይመስለኛል። በአጭሩ በዓሉ የደራሲነት ሙያውን የሠራበትና በብዕር የተፋለመ የሃቅ አርበኛ ነው" ብለዋል።



በርግጥ "ደራሲው" በተሰኘው ልብ ወለድ መጽሐፉ የፈጠረው "ሲራክ" የተባለው ገጸ

ባሕሪ በዓሉ ራሱ ካልሆነ ማን ሊሆን ይችላል? ያም ሆነ ይህ ግን እንዲህ ዓይነቱን ጥያቄ ለመመለስ በሚደረገው ጥረት እንደ ወጣ ቀርቶ የተሰወረው በዓሉ በሲራክነት እየተነበበ ይደምቃል።

በዓሉ በሲራክ አንደበት የሚለን "የምንኖረው የዱቤ ኑሮ ነው እንዲህ ከሆነ ደግሞ ይኸን ያህል መጨነቁ ለምንድን ነው?" እናም የግለ ታሪኩን መቅድም በደራሲው አስቃኝቶን መደምደሚያውን በኦሮማይ "ሲላቪ" ወይም በቃ!! ብሎ ያነጠበ ይመስላል።

ታዲያ በዓሉን ከሌሎች ደራሲዎች ልዩ ከሚያደርጉት ነገሮች መካከል አንዱ ድርሰቱም ደራሲውም እኩል "ስቅ" ያላቸው መሆናቸው ነው።

በዓሉ ግርማ ወልዴ የፊቱ ቀለም የቀይ ዳማ፣ መልከ መልካም፣ ቁመናው መካከለኛና በአለባበሱ ሽቅርቅር ሆኖ የሚታይ ሰው ነበር።

## መወድስ

**ብዕር ከሰይፍ ይልቅ ምንኛ ስለታም**
**እንኳን ለጠላቱ ለታጣቂ አይሳሳም**
**የበዓሉ ብዕር አብሮት ኖሮ ኖሮ**
**በአምስት ማኀደር አቅልሞ ተናግሮ**
**በስድስተኛው ድምጽ በኦሮማይ ደፍሮ**
**የብዕሩ ስለት ወጋው እሱን ዞሮ**
**'ሴ ላቪ' ቻዎ! አለ በብዕሩ ክብሮ**





## ትምህርተ ውልብታ

**ለእውነት መቆም የሚያስከፍለው ዋጋ ተመኑ ሕይወትን እስከ መሰዋት ይደርሳል።**

**«ጋዜጠኛ ዝነኛ ደራሲ ሊሆን አይችልም» የሚለውን ያረጀ አስተሳሰብ መሻር ከቻሉት ጥቂት ደራሲ ጋዜጠኞች መካከል አንዱ በዓሉ ግርማ ነው።**





## የውልብታ ምንጭ


Molvaer, Reidulf K., *Black Lions: The Creative Lives of Modern Ethiopia's Literary Giants and Pioneers,* Lawrenceville: The Red Sea Press, Inc., 1997

Taddesse Adera and Ali Jimal Ahmed (Editors), *Silence is not Gold: a Critical Anthology of Ethiopian Litrature* Lawrenceville: The Red Sea Press, Inc., 1995

*ታደሰ ቴሌ ሳልቫኖ የአናብስት ምድር፣ የኢትዮጵያ ሥራዊት የታሪክ ዘገባ ከ1927 እስከ1983 ዓ.ም.* ሮም ማተሚያ ድርጅት 1999 ዓ.ም.

*በዓሉ ግርማ የቀይ ኮከብ ጥሪ* 1972 ዓ. ም.

*በዓሉ ግርማ ኦሮማይ የመጀመሪያ እትም ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት አዲስ አበባ*1975 ዓ.ም.

*ፀደይ መጽሔት ህዳር ወር* 1989 ዓ.ም.

*ኢንፎቴይመንት መጽሔት ጥቅምት ወር* 1997 ዓ.ም.

*ቃለ ምልልስ ከደራሲና ጋዜጠኛ አንዳርጌ መስፍን ጋር የተካሄደ መጋቢት* 6 *ቀን* 1999 ዓ.ም.

*ቃለ ምልልስ ከጋዜጠኛ ይመኑ ይርዳው ጋር የተደረገ የካቲት* 21 *ቀን* 1999 ዓ.ም.

*ቃለ ምልልስ ከደራሲና ማሞ ውድነህ ጋር አርብ የካቲት* 23 *ቀን* 1999 ዓ.ም

*ኤፍ.ኤም ሬድዮ የቅዳሜ ጨዋታ ዝግጅት ከሐያሲ እና ደራሲ አስፋው ዳምጤ ጋር የተደረገ ቆይታ፤ ታህሳስ* 14 *ቀን* 1999 ዓ.ም.






## የአንባቢው የግል ማስታወሻ

